# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

81ኛ ዓመት ቁጥር 364 ጳጉሜን 4 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ







## «መስዋዕትነት ከፍለን ሰላም የምናስከብረው ጦረኛ ስለሆንን ሳይሆን ለሰላም የማንከፍለው ዋጋ ስለሌለን ነው»

- አቶ ብናልፍ አንዷለም
የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር

ፎቶ፡- ሀይሉ አብርሃ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- እኛ ኢትዮጵያውያን መስዋዕትነት ከፍለን ሰላም የምናስከብረው ጦረኛ ስለሆንን ሳይሆን ለሰላም የማንከፍለው ዋጋ ስለሌለን ነው ሲሉ የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ብናልፍ አንዷለም ተናገሩ።

"ሰላም ለኢትዮጵያ" በሚል መሪ ሃሳብ የተዘጋጀ የፓናል ውይይት በትናንትናው ዕለት ተካሂዷል። በትናንትናው ዕለት የተከበረው የሰላም ቀን በዓል አስመልክቶ የተካሄደው የፓናል ውይይት የሀገር ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት አባቶች የጋራ ምርቃትና ፀሎት ነው የተጀመረው።

«መስዋዕትነት ከፍለን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



## ትህነግ ሸኔን በመጠቀም የብሄር ግጭት በመፍጠር ሀገር ለማፍረስ ያደረጋቸው ተደጋጋሚ ሙከራዎች ከሽፈዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ትህነግ የራሱን ቅጥረኞች እና የሸኔን አሸባሪዎች በመጠቀም ብሔር ላይ ያነጣጠረ ጥቃት በማድረስ አንዱን ብሔር በሌላው ላይ ለማስነሳት ተደጋጋሚ ሙከራዎችን ቢያካሂድም በጸጥታ ኃይሉ ጠንካራ ክንድ እና በህብረተሰቡ ትብብር በመመታቱ ዓላማው ሳይሳካ መቅረቱን የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ገብረ ሚካኤል ተናገሩ።

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ገብረ ሚካኤል፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ባዘጋጀው

ትህነግ ሸኔን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## «በአንድ እጃችን ክላሽ በሌላ እጃችን ዶማ ይዘን በማልማት ጠላቶቻችንን እያሸነፍን ነው»

- የወልቃይት ጠገዴ የአርሶ አደር ሚሊሻዎች

**ሙሉቀን ታደገ**

አዲረመጥ ፡- በአንድ እጃችን ክላሽ በሌላ እጃችን ዶማ ይዘን የግብርና ሥራዎቻችንን በማሳለጥ ጠላቶቻችንን እያሸነፍን ነው ሲሉ የወልቃይት ጠገዴ የአርሶ አደር ሚሊሻዎች ተናገሩ።

በወልቃይት ጠገዴ አዲረመጥ ከተማ ዙሪያ ነዋሪ የሆነው አርሶ አደር ሚሊሻ ዘነበ ስዩም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው የህወሓት የሽብር ቡድን ከ40 ዓመታት በላይ በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ላይ የከፋ በደል ሲያደርስ ኖሯል። ይህ በደሉ አልበቃው ብሎ አሁን ላይ ደግሞ አርሶ አደሩ አርሶ እና አምርቶ ቤተሰቦቹን ማስተዳደር እንዳይችል ለማድረግ የክረምት

«በአንድ እጃችን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ፎቶ - እዮብ ተፈራ





ፎቶ፡- ሀይሉ አብርሃ

## ዕለቱ አገልጋይነት ፀጋ መሆኑን በሚያሳዩ ተግባራት ይከበራል

ገጽ 6






ግድቡን ለማጠናቀቅ 60 ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል

## ሕብረተሰቡ ለዓባይ ግድብ ሲያደርግ የቆየውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ተጠየቀ

ገጽ 3

# ማህበሩ ለበዓል አስር ሺህ የቁም እንስሳት አቀረበ

**ሙሳ ሙሐመድ**



አዲስ አበባ፡- ለመዲናዋ ዓመት በዓል እርድ አገልግሎት የሚውሉ አስር ሺህ የቁም እንስሳትን ማቅረቡን የኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ነጋዴዎች ማህበር አስታወቀ።

የኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ነጋዴዎች ማህበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ መዓዛ ቀለመወርቅ እንደተናገሩት፣ በበዓሉ የቁም እንስሳት እጥረት እንዳይኖር ከተለያዩ ክልሎች ወደ አዲስ አበባ በማስገባት ላይ መሆኑን አስታውቀዋል።

የእርድ እንስሳቱን በማጓጓዝ ሂደት ክፍተት እንዳይፈጠርና የሥጋ አቅርቦቱ እንዳይታወክ ለማድረግም ከህግ፣ ከጸጥታና ሰላም አስከባሪ አካላት ጋር ሙሉ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል።

በተያያዘም የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ለ2015 የዘመን መለወጫ በዓል ሰባት ሺህ የበሬ፣ የበግና ፍየል ዕርድ እንደሚያከናውን የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሰይድ እንድሪስ አስታውቀዋል።

የዕርድ ሥራውን ለማቀላጠፍ ከቋሚ ሠራተኞች በተጨማሪ ጊዜያዊና የኮንትራት ሠራተኞችን በመቅጠርና ሥጋውን የሚያሰራጩ ተሽከርካሪዎችን ፈትሾ ማዘጋጀቱን አቶ ሰይድ ገልጸዋል።

ህብረተሰቡ ከህገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድና የሥጋ ዝውውር ራሱን እንዲጠብቅም ሥራ አስኪያጁ አሳስበዋል።

አቶ ሰይድ አያይዘውም ህብረተሰቡ የቄራዎች ድርጅት ካከራያቸው ሱቆችና ከሉኳንዳ ቤቶች የተመረመረና ጤናማነቱ የተረጋገጠ ሥጋ መግዛት እንዳለበትም መክረዋል።

በድርጅቱ የበሬ ሥጋ በኪሎ በ435 ብር፣ የፍየል ስጋ 310 ብር እና የበግ ስጋ 300 ብር ተምኖ ለመሸጥ መዘጋጀቱንም አቶ ሰይድ አስታውቀዋል።

በበዓሉ ዕለትም ሙሉ በግና ፍየል እንደሚሸጥም ሥራ አስኪያጁ ጠቁመው፣ በግል የእንስሳት እርድ አገልግሎት የፈለጉ ካሉ ድርጅቱ ድረስ በማምጣት አገልግሎቱን ማግኘት እንደሚችሉም አስረድተዋል።

የአዲስ አበባ ሉኳንዳ ነጋዴዎች ማህበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አየለ ሳህሌ በበኩላቸው፣ የበዓል ስጋ አቅርቦት ላይ በመዲናዋ በሁሉም አካባቢዎች የተሻለ የሥጋ አቅርቦት እንዲኖር እየሰራን ነው ብለዋል።

ሁሉም ነዋሪ የሚፈልገውን ያህል ደህንነቱ የተጠበቀ፣ የሥጋ አቅርቦት እንዲያገኝ የሚያስችለንን ዝግጅት አድርገናል፣ በእለቱም ምንም ዓይነት የስጋ አቅርቦት ችግር እንዳይኖር ለማድረግ እየሰራን ነው ብለዋል አቶ አየለ።

የአዲስ አበባ ምግብ መድኃኒት ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የምግብና መጠጥ ዘርፍ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ትግስት በዳዳ፣ የበዓል መቃረብን ተከትሎ በምግብ ማምረቻና ማከፋፈያ፣ አገልግሎት መስጫና ችርቻሮ ተቋማት ላይ በተካሄደው መደበኛ የቁጥጥር ሥራ 4449 ጉድለት ተገኝተው የእርምት እርምጃ ተወስዶባቸዋል ብለዋል።

በዚህም ከሰባት ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ 191 ሺህ 266 ኪሎግራም የምግብ ነክ እና ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ የ74 ሺህ 90 ሊትር የመጠጥ ግብዓቶች ተወግዷል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ወይዘሮ ትግስት ገለጻ፣ በአጠቃላይ በመዲናዋ ወደ ህብረተሰብ ቢራጭ የጤና እክል ጉዳትን የሚፈጥሩ በገንዘብ ቢገመቱ 36 ሚሊዮን 505 ሺህ 598 ብር የሚያወጡ ምግቦች፣መጠጦችና የምግብ ማብሰያ፣ ማቅረቢያና ማሸጊያ መሳሪያዎች በተደረገው የቅድመ ቁጥጥር ሥራ እንዲወገዱ ተደርጓል።

ጥራቱንና ደህንነቱን ያልተጠበቀ ህገ-ወጥ የምግብ ክለሳ፣ ፈዋሽነቱ ያልተረጋገጠ የመድኃኒት ዝውውርንና ሽያጭ፣ ህገ-ወጥ የቁም እንስሳት እርድንና ስጋ ሽያጭ ተግባራት በበዓል ወቅት ሊከሰቱ ስለሚችሉ ህብረተሰቡ እራሱን እንዲከላከልም አሳስበዋል።



# «ስናብር ስናምር» የተሰኘ የሙዚቃ ሲዲና ቪዲዮዎች ስብስብ ለሀገር መከላከያ ሰራዊት ተበረከተ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የአንድነት ቀንን ምክንያት በማድረግ ኢትዮጵያውያን አርቲስቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰርተው ያጠናቀቁትን "ስናብር ስናምር" የተሰኘ የሙዚቃ ሲዲና ቪዲዮዎች ስብስብ ለኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት አበረከቱ።

በርክክብ ስነስርዓቱ ላይ የኢፌዴሪ መንግሥት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ከበደ ዴሲሳ እንደተናገሩት፤ በሀገር ጉዳይ ላይ አንድ የመሆን ነገር ከምንም በፊት ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ነው፤ ሀገራዊ አንድነትን ማረጋገጥ ማለት ክብርን ማረጋገጥ ማለት ነው።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ ሰላማዊና የፀናች ሀገርን ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ እና ህብረብሄራዊ አንድነትን ለማስጠበቅ መሰል ሥራዎች ከአርቲስቶች ይጠበቃሉ ብለዋል።

ሁሉም በያለበት የሥራ ድርሻ ሀገራዊ አንድነትን በሚያስጠብቁ ሥራዎች ላይ ትኩረቱን በመስጠት ማገልገል እንደሚጠበቅበትም ጨምረው ገልጸዋል።

የሙዚቃ አቀናባሪው ካሙዙ ካሳ በርክክቡ ወቅት እንደገለፀው፤ ይህን ሲዲ ለጀግናው መከላከያ ሰራዊት ሲያስረክብ እንዲሁም የዚህ አኩሪ ተጋሪ በመሆኑ ኩራት እንደሚሰማው ተናግሯል።

የካሴቱ አስተባባሪ ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ ባዬ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ አንድነት ደካማነትን ያሸንፋልና መሰል የኪነጥበብ ሥራዎች በመልካም ጎናቸው ታሪክ ሲያወሳቸው የሚኖር ነው።

ረዳት ፕሮፌሰሩ በገለፃቸው ሲዲው ውስጥ የተካተቱት ዘፈኖች በተለያዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የተሰሩና ብዝሀነት የሚታዩባቸው ናቸው ብለዋል።

አርቲስቶቹ ስለ አንድነት፣ ሰላም፣ ፍቅር እና መተሳሰብ የሚሰብኩ የሙዚቃ ሥራዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰርተው በማጠናቀቅ የአንድነት ቀን አዘጋጅ ኮሚቴዎች በተገኙበት ለመከላከያ ሚኒስቴር አስረክበዋል።

የሙዚቃ ክሊፑ አምስት የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን (ቪዲዮዎችን) የያዘ ሲሆን፣ ሥራዎቹ ብዝሃነትን በሚያንጸባርቅ መልኩ የተሰሩ መሆናቸው ተመላክቷል።

በዝግጅቱ ላይ የመከላከያ ሚኒስትሩ ዶክተር አብርሀም በላይን ጨምሮ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ፣ አርቲስቶች እንዲሁም ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው አካላት ተገኝተዋል።




# የከተማዋን የቱሪዝም ዘርፍ የሚያነቃቃ የእግር ኳስ ውድድር ሲካሄድ ነው

**የሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የባህር ዳር ከተማን የቱሪዝም ዘርፍ የሚያነቃቃ የእግር ኳስ ውድድር "የአማራ ባንክ - ጣና ዋንጫ" በሚል ሥያሜ ሊካሄድ መሆኑ ተገለጸ።

የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት መምሪያ ኃላፊ አቶ አብርሃም አሰፋ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፣ ውድድሩ በኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ክለቦችና በአፍሪካ ሀገራት ክለቦች መካከል የሚካሄድ ነው። ይህም የባህር ዳር ከተማን የቱሪዝም ዘርፍ የሚያነቃቃ የእግር ኳስ ውድድር እንዲሆን አስችሎታል።

ውድድሩ መስከረም 6፣ 2015ዓ.ም በይፋ እንደሚጀመር የገለጹት አቶ አብርሃም፣ የአማራ ባንክ የስፖርቱን ዘርፍ በመደገፍ የትውልድን ጤና የመጠበቅ፣ ወዳጅነትን የማጠናከርና የቱሪዝም ዘርፉን በማነቃቃት ማህበረሰቡን የመጥቀም ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ ይገኛል ብለዋል።

ከአፍሪካ ሀገራት የሚመጡ ተጫዋቾች የባህር ዳር ከተማን ተዘዋውረው የሚጎበኙበት ሁኔታ እንደሚመቻች የገለጹት ኃላፊው፣ ውድድሩ የባህር ዳር ከተማን ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ውበት ለማስተዋወቅ የሚያስችል ነው ብለዋል።

እንደ አቶ አብርሃም ገለጻ፣ ከ37 በላይ ደሴቶችና ከ19 በላይ ገዳማትን አቅፎ የያዘው ጣና ኃይቅንና በልዩ ገጽታው ሐሴት የሚያጎናጽፈው ጢስ አባይ ፏፏቴን ለመጎብኘት ክለቦቹ ከነደጋፊዎቹ እንደሚሄዱ ይታሰባል። በዚህም ውድድሩ ለባህር ዳር ከተማና ለአካባቢዋ ነዋሪ ውድድሩን የመሳተፍና የሥራ አማራጭ እድሎች እንደሚኖርም ተናግረዋል።

ስፖርት የማህበረሰብን አዕምሮና አካል ያጠናክራል ያሉት አቶ አብርሃም፣ ውድድሩ ከሚፈጥረው መልካም መስተጋብርና አብሮነት ባሻገር የከተማዋንና የአካባቢውን የቱሪዝም ዘርፍ ለማነቃቃትና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋል።

የአማራ ባንክ ማርኬቲንግና ብራንዲንግ ዳይሬክተር አቶ አስቻለው ታምሩ በበኩላቸው ባንኩ ይህ ታላቅ ውድድር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲዘጋጅ ኩነቱ ለማህበረሰቡ የሚያስገኘውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ በማሰብ ነው ብለዋል። በዚህም በኢትዮጵያ ቤቲንግ ሊግ የሚጫወቱ ክለቦችና የአፍሪካ ሀገራት ክለቦች የሚሳተፉበት የእግር ኳስ ውድድር ይሆናል።

ለመጀመሪያ ጊዜ በባህር ዳር ዓለም አቀፍ ስታዲየም የሚዘጋጀው የስፖርት ውድድር "የአማራ ባንክ - ጣና ዋንጫ" በሚል ሥያሜ ይካሄዳል ያሉት አቶ አስቻለው፣ የአማራ ባንክ ይህን ውድድር ያዘጋጀው በስፖርት የትውልድን ጤንነት፣ አብሮነትና ወዳጅነት ለማስቀጠል፣ በቱሪዝም ዘርፉ ደግሞ የከተማዋን ኢኮኖሚ በማነቃቃት ማህበረሰቡን ተጠቃሚ በማድረግ "ከባንክ ባሻገርነቱን" ከሚገለጥባቸው መንገዶች አንዱ በመሆኑ ነው ብለዋል።

የአማራ ባንክ የፋይናንስ ተቋም ከመፍጠር ባለፈ ለማህበረሰብ ለውጥ አሻራውን በማሳረፍ ድርሻውን ለመወጣት የተቋቋመ እንደሆነ ይታወቃል ያሉት አቶ አስቻለው፣ በዚህም ባንካችንን በቀጣይ የሚሰራቸው ዘርፈ ብዙ የማህበረሰብ ተኮር ተግባራት ለመሥራት አቅዷል ብለዋል።

እንደ አቶ አስቻለው ገለጻ፣ በምረቃው እለት በአዲስ አበባና ዙሪያው የአንበሳ አውቶቡስ ተጠቃሚዎች ከንጋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ ሶስት ሰዓት ሙሉ ክፍያውን ሸፍኖ እንዲጓጓዙ አድርጓል። በተመረጡ ሆስፒታሎች በእለቱ ለተወለዱ እናቶች የ"እንኳን ደስ አላችሁ" ስጦታ ሰጥቷል።



# ክልሉ ለመከላከያ ሰራዊት የ101 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አደረገ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ክልል ለሃገር መከላከያ ሰራዊት የበዓል መዋያ የሚሆን የ101 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አደረገ። ሁሉም ዜጋ አካባቢውን በንቃት በመጠበቅና ለመከላከያ ሰራዊት ድጋፍ በማድረግ የአሸባሪውን እኩይ ተግባር ማክሸፍ እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል።

በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ መስከረም ደበበ ድጋፉን ሲያስረክቡ እንደገለጹት፤ በአሸባሪው የሕወሓት ቡድን አገርን የመዳፈር፣ ሕዝብን የመውረር ሁኔታ በሰላም እንዲፈታ መንግሥት የሰላም እጅን ቢዘረጋም አሸባሪው የሰላምን እጅ በማጠፍ ለሶስተኛ ጊዜ አገራችን ወሯል። ወረራውን ለመቀልበስ ጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችንና ጥምር ጦሩ የሚያደርገውን ተጋድሎ ለመደገፍ የኦሮሚያ ዞኖች፣ ሕዝቦች፣ ባለሀብቶችና ልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ሰራዊቱ በዓል እንዲያከብር አስፈላጊ ነገሮችን ድጋፍ አድርገዋል።

መከላከያ ሰራዊቱ በዓሉን ባለበት ግንባር እንዲያከብር አጠቃላይ ድምር ዋጋ 101 ሚሊዮን ብር የሚገመቱ የተለያዩ ድጋፎችን አድርገዋል ያሉት ኃላፊዋ፤ 1329 ሰንጋ፣ 200 በግና ፍየሎች፣ ደረቅ ሬሽን፣ የምግብ ጥራጥሬዎችን፣ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ተበርክተዋል። እንዲሁም ሁለት መቶ ሰባት ኩንታል በሶ፣ ሰማኒያ አራት ኩንታል ቆሎ፣ መቶ ኩንታል ዱቄት፣ ሶስት መቶ ሰባ አምስት ኩንታል መኮሮኒ፣ አንድ ሺህ ሰባት መቶ 15 ኩንታል ሩዝ፣ ዘጠና አምስት ካርቶን ፓስታ፣ አርባ ካርቶን የጽዳት እቃዎች የተደረጉ ድጋፎች መሆናቸውን ገልጸዋል።

እንደ መስከረም ገለጻ፤ ድጋፉ የመጀመሪያ እንጂ የመጨረሻ አይደሉም። በቀጣይ የኦሮሚያ ክልል ከሰራዊቱ ጎን በመሆን አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ያደርጋል። የክልሉ ነዋሪዎች የአገራቸው ሉአላዊነት ሲነካና የሕዝብ ሰላም ሲደፈርስ ቀፎውን እንደተነካ ንብ ተነስተው ለሰራዊቱ ደጀን በመሆን ያግዛሉ ብለዋል።

የመከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ማርታ ሉዊጂ ድጋፉን ሲቀበሉ እንደገለጹት፤ ሁሉም ዜጋ አካባቢውን በንቃት በመጠበቅ የአሸባሪውን እኩይ ተግባር በማክሸፍ ለኢትዮጵያ አንድነት መቆም ያስፈልጋል። የኦሮሚያ ክልል ግንባር ላለው ሰራዊት ያደረገው ድጋፍ ለሰራዊቱ ያለውን አጋርነቱን ያሳየበት መሆኑን ገልጸዋል።

ሰራዊቱ በዓሉን እንዲያሳልፍ የተደረገው ድጋፍ ከፍተኛ ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ የኦሮሚያ የሴቶች አደረጃጀት ከዚህ ቀደም ከፍተኛ ድጋፍ ሲያደር እንደነበር ገልጸው አመስግነዋል። ሰራዊቱ ባለበት አገሩን እየጠበቀ በዓሉን እንዲያሳልፍ በማሰብ የተደረገው ድጋፍ ለሰራዊቱ ትልቅ የሞራል ስንቅ እንደሚሆን ተናግረዋል። አሸባሪው እስኪደመሰስ የሚደረጉ ድጋፎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉም ጠይቀዋል።

የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለማስጠበቅ ሁሉም መረባረብ እንዳለበት የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለበት ወታደር ነው፤ ግማሹ ግንባር ይዋጋል፣ የተቀረው ያመርታል፣ ስንቅ ያዘጋጃል፣ ይማራል፣ ይመራመራል፤ ሌላው የወደፊት የኢትዮጵያን ትልም በማውጣት ለኢትዮጵያ አንድነት ይዋደቃል ብለዋል።

ግድቡን ለማጠናቀቅ 60 ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል

# ሕብረተሰቡ ለዓባይ ግድብ ሲያደርግ የቆየውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ተጠየቀ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ ግንባታን በተያዘለት ጊዜ ከዳር ለማድረስ ሕብረተሰቡ የጀመረውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ተጠየቀ። ግድቡን ለማጠናቀቅ ሁለት ዓመት ከ6 ወር እንደሚወስድ እና 60 ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግም ተጠቁሟል።

የግድቡ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት 14ኛ መደበኛ ጉባኤውን ትናንት በሸራተን አዲስ ባካሄደበት ወቅት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትሩ አቶ ተስፋዬ በልጅጌ እንደተናገሩት፤ ፕሮጀክቱ በርካታ መስዋትነት የተከፈለበት ሲሆን በአሁኑ ጊዜም ወደ ወሳኝ ምዕራፍ ተሸጋግሯል።

ኢትዮጵያውያን በጋራ ከቆሙ የትኛውንም ጫና ተቋቁመው ለአገር ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ፋይዳ ያለው ፕሮጀክት መገንባት እንደሚችሉ ማሳያ ነው ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ እንደ አገር የተጀመረው የለውጥ ሥራ ውጤታማነት ጎልቶ ከወጣባቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ የዓባይ ግድብ አንዱ እንደሆነና አሁን ላይ ወደ ማይቀለበስበት ደረጃ መድረሱንም ጠቁመዋል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትርና የብሔራዊ ምክር ቤት ጽህፈት ቤቱ ምክትል ሰብሳቢ ዶክተር ሀብታሙ ኢተፋ፤ ኢትዮጵያ ከውስጥና ከውጭ በደረሰባት ተጽዕኖ ውስጥ ሆና ሶስተኛው ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቅና ሁለተኛው ተርባይን ሃይል ማመንጨቱ የአሸናፊነታችንና የአይበገሬነታችን መገለጫ ነው። ህዝቡ ገንዘቡን ከማውጣት ባሻገር በዲፕሎማሲው መስክ ጠንካራ ትግል አድርጓል፤ የታየው ስኬት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ስኬት ነው። ግድቡን ለማጠናቀቅ የሁሉም ዜጋ ርብርብ ያስፈልጋል ብለዋል።



ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ

የግድቡ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አረጋዊ በርሄ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያን ለማንበርከክ ጠላቶቻችን ከውስጥና ከውጭ በመናበብ የሚያደርጉትን ሩጫ በአንድነትና በህብረት ማሸነፍ ችለናል። በግድቡ የታየው ታሪክ የመስራት ሂደት በተከታታይና በማያቋርጥ መንገድ መቀጠል አለበት ሲሉ ገልጸዋል።

የዓባይ ግድብ ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ ግድቡ አጠቃላይ ያለበትን ደረጃ ያብራሩ ሲሆን የብረታብረት ግንባታው 73 ነጥብ 3፣ የኮርቻው ግንባታ 99 ነጥብ 6፣ የሲቪል ሥራው 96 ነጥብ 2 ከመቶ ደርሷል። ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ 60 ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል። ለዚህም የተደራጀ የህዝብ ተሳትፎ ሊኖር ይገባል ብለዋል።

ዋና ሥራ አስኪያጁ አጠቃላይ አፈፃፀም 88 በመቶ መድረሱን ጠቁመው፤ ግድቡ በሁለት ዩኒት ኃይል ማመንጨት መቻሉና የግድቡ 3ኛ ዙር የውሃ ሙሌት የ2014 ወሳኝ የሥራ ክንውኖች እንደሆኑም ተናግረዋል። ፕሮጀክቱን በ70 ቢሊዮን ብር ለማጠናቀቅ ታቅዶ የተጀመረ ቢሆንም በግብዓት እቃዎች ዋጋ መናርና በተለያዩ ምክንያቶች እስከ ሐምሌ 2014 ብቻ የወጣው ገንዘብ 172 ቢሊዮን ብር ደርሷል ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ አጠቃላይ ግድቡን ለማጠናቀቅ የሚወስደው ገንዘብ 232 ቢሊዮን ብር ይሆናል ብለዋል።

የግድቡ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ታገል ቀኑብህ በ2015 በጀት ዓመት ለግድቡ ግንባታ 18 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ መታቀዱን ጠቁመው፤ የተጠናከረ የአካባቢ ጥበቃ ሥራም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

በጉባኤው የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት የግድቡ ግንባታ ያለበት ደረጃ መልካም መሆኑን ጠቁመው፤ ግድቡን ለማጠናቀቅ የውጪውን ጫና ለመመከት በዲፕሎማሲው ዘርፍ ጠንካራና የተናበበ ሥራ መስራት እንዳለበት አሳስበዋል።

# ባንኩ ለመቄዶንያ ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አደረገ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- የአባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር ለመቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል የገንዘብ ድጋፍና የምሳ ግብዣ ፕሮግራም አካሄደ። ባንኩ የ2015 ዓ.ም አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግ ለማዕከሉ የሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር ድጋፍ፣ አልባሳት እንዲሁም የማዕድ ማጋራት መርሐ ግብር አድርጓል።

የባንኩ ማኔጅመንት አባላት በማዕከሉ በመገኘት የማዕከሉን የሥራ እንቅስቃሴ እንዲሁም ተረጅ ወገኖች ያሉበትን ሁኔታ በማስመልከት ጉብኝት አድርገዋል።

የባንኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ የኋላ ገሰሰ የመቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል እያከናወነ ያለውን ተግባር አድንቀው፣ ባንኩ የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታትና ማህበራዊ ኃላፊነት ለመወጣት እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

ዓባይ ባንክ የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት በበርካታ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት እየተሳተፈ ሲሆን በተለይም በትምህርት፣ በጤናና በሌሎች ማህበራዊ ኃላፊነቶች ላይ ተቋማዊ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን በማድረግ ላይ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

ይህን መሰረት በማድረግም ለማዕከሉ ባንኩ የማዕድ ማጋራትና የአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር ፣ የባንኩ ሰራተኞች ደግሞ የአንድ ሚሊዮን ብር ድጋፍ ማድረጋቸውን ዋና ሥራ አስፈፃሚው አስታውቀዋል።

ባንኩ የማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት በቀጣይም ከማዕከሉ ጋር አብሮ ለመስራትና አቅም በፈቀደ መጠን ለማዕከሉ የሚያስፈልገውን ድጋፍ አጠናክሮ ለመቀጠል መወሰኑን አቶ የኋላ ተናግረዋል።

የማዕከሉ መስራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ቢኒያም በለጠ በበኩላቸው ባንኩ ላደረገው በጎ አድራጎትና ድጋፍ አመስግነው ሌሎች ተቋማት የዚህን ባንክ ፈለግ በመከተል ማዕከሉን በተለያየ መልኩ በመደገፍ የማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

ማዕከሉ አርባ በሚሆኑ ድጋፍ የሚሹ ወገኖች ጀምሮ አሁን ከ7ሺህ 500 በላይ ተረጂዎች እስኪደርስ ድረስ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ሆኖ ወገኖችን እየረዳ ዛሬ ላይ መድረሱን አስታውሰው ይህም የሆነው ለማዕከሉ ድጋፍ የሚያደርጉ ወገኖች በመኖራቸውና በፈጣሪ እገዛ መሆኑን ተናግረዋል።






ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

ማዕከሉ በተለያዩ የክልል ከተሞች በማስፋፋት በየአካባቢው የማዕከሉን እርዳታ የሚሹ ወገኖችን ባሉበት ለመርዳትና የተረጂዎችን ቁጥር እስከ ሃያ ሺህ ለማድረስ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ በመሆኑ እንዲህ አይነቶቹ ድጋፎች ለማዕከሉ እጅግ የሚያስፈልጉ መሆኑን ተናግረዋል።

የተለያዩ ተቋማት አውደ ዓመትን ጨምሮ ሌሎች ልዩ ልዩ ዝግጅቶቻቸውን በማዕከሉ በማሳለፍ፣ ልዩ ድጋፎችን በማድረግ እንዲሁም ማንኛውንም በጎ ተግባር በመከወን ማዕከሉን በተለያየ መልኩ መደገፍ የሚቻል መሆኑን ገልፀው፣ ኢትዮጵያውያን በዚህ በጎ አድራጎት ተግባር የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አሸባሪው ሕወሓት የሕዝብ ጠላት መሆኑን በገሃድ አረጋግጧል!

አሸባሪው ሕወሓት ኢትዮጵያን ባስተዳደረባቸው 27 ዓመታት ጭምር መንግስታዊ ሽብርተኝነትን በማካሄድ የሚታወቅ ቡድን ነው። ቡድኑ በመንግስት መዋቅር የሚታገዝ የዘረፋ ቡድን ከማቋቋም ጀምሮ በዘረፋ የሚያገኘውን ሃብት በህዝቦች መካከል ጸንቶ የቆየውን አንድነትና አብሮነት በመናድ እርስ በእርስ ለማጫረስ ሲጠቀምበት ኖሯል።

በስልጣን ዘመኑ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች መንግስታዊ ሽብርተኝነትን በማፋፋም በየአካባቢው ሁከትና ብጥብጥ እንዲነሳና አልፎ ተርፎም የብሄር እና የሃይማኖት ግጭት እንዲቀጣጠል በማድረግ ኢትዮጵያ በሂደት እንድትፈርስ ረጅም ርቀት ተጉዟል። በጉራ ፈርዳ አማራዎች ላይ ያነጣጠረ ጥቃት እንዲደርስ በማድረግ ብሄር ተኮር ግጭት ለማስነሳት ሞክሯል። በጋምቤላ በአኝዋክና በኑዌር ጎሳዎች መካከል ግጭትን በመቀስቀስ በርካቶች እንዲያልቁ ምክንያት ሆኗል። በቤኒሻንጉል የጉሙዝ ታጣቂዎችን በአማራ ብሄር ተወላጆች ላይ በማነሳሳት ጥቃት እንዲፈጽሙ ድጋፍ ሲያድርግ ቆይቷል።

በኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎች ኦነግ ናችሁ በሚል ሽፋን በርካቶችን ለማይሽር ስቃይና መከራ ድርጓቸዋል። በኦነግ ስምም የተለያዩ የሽብር ድርጊቶችን በማቀነባበር በርካታ ንጹሃን እንዲሞቱ አድርጓል። በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልልም አብረው የኖሩ ህዝቦችን በማጋጨት የስልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ሞክሯል። በአፋርና ሶማሌ መካከል የማያባራ ግጭትና ሁከት በመፍጠር ሁለቱ አካባቢዎች ዘላለማዊ ቅራኔ ውስጥ እንዲገቡ አበክሮ ሰርቷል። በአማራ ክልልም አማራን በጠላትነት ከመፈረጅ አንስቶ በቅማንት፤ በአገውና በኦሮሚያ ልዩ ዞን የተለያዩ ግጭቶችን በመጠንሰስ ክልሉ በግጭት አዙሪት ውስጥ እንዲኖር ለማድረግ ሞክሯል።

ሆኖም አስተዋይ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቡድኑ የሚሸረቡ ሴራዎችን በጥበብ በማለፍ ቡድኑን ከመንበረ ስልጣኑ በማሽቀንጠር የአገዛዝ ቀንበሩን ማስወገድ ችሏል።

የሕወሓሃት የሽብር ቡድን በህዝብ ተቃውሞ መቀሌ ለመመሸግ ከተገደደ በኋላ እኔ የማልመራት ኢትዮጵያ ትፍረስ በሚል ከልክ ያለፈ ራስ ወዳድነት እና የስልጣን ጥማት በየአካባቢው የሽብር ተግባራትን ሲጠምቅ ቆይቷል። ዩኒቨርሲቲዎች ጭምር የሽብር ማዕከል በማድረግ የነገ አገር ተረካቢ ወጣቶችን ህይወት ቀጥፏል።

የሕወሓት የሽብር ቡድን ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲኦል ድረስም ቢሆን እወርዳለሁ በማለት በይፋ አገር ከሃዲነቱን ከማሳየቱም በተጨማሪ የኢትዮጵያን መንግስት ለመጣል ታሪካዊ የሚባሉ ጠላቶች ከሚባሉት አገራት ጋር ጭምር እየሰራ መሆኑንም ያለ ማፈረር በአደባባይ ለፍፏል። አሁን ደግሞ ሰሞኑን ከሽብር ቡድኑ የወጣ አንድ ሰነድ በግልጽ እንዳሳየው ሕወሓት ከአልሸባብ የሽብር ቡድን ጋር እየሰራ መሆኑንም አጋልጦታል።

ነሃሴ 8 ቀን 2014 ከሽብር ቡድኑ አፈትልኮ በወጣውና ‹‹የማጠቃለያ ምዕራፍ አካሄድና ስትራቴጂ›› በሚለው ሰነድ ላይ እንደተመላከተው አልሸባብና ሕወሓት ኢትዮጵያን የማተራመስ የጋራ ዕቅድ ነድፈው ሲነቀሳቀሱ መቆየታቸው ግልጽ ሆኗል። ይህንኑ መሰረት በማድረግም አልሸባብ ኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ለማድረስ ሞክሯል።

አልሻባብ ከአሸባሪዎቹ ሕወሓትና ሸኔ ጋር በፈጠረው ኅብረትም በሶማሌ ክልል በኩል ሾልኮ በመግባት አገሪቱን የሽብር ማዕከል ለማድረግ ሙከራ ቢያደርግም በሶማሌ ክልል ልዩ ኃይልና በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ቅንጅት ቡድኑ አሳፋሪ ሽንፈትን ተከናንቦ ለወሬ ነጋሪ ሳይቀር በሙሉ ተደምስሷል። ቡድኑ በኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይሎች ከፍተኛ አመራሮቹን ከማጣቱም በላይ በርካታ አባላቱም ተደምስሰዋል።

የአሸባሪው ሕወሓት ሴራ በተጋለጠበት የቅርብ ጊዜ ሰነድ የሽብር ቡድኑ የኢትዮጵያን ሰላምና ዕድገት ከማይመኙ ማናቸውም ባዳና ባንዳ አሸባሪዎች ጋር በመሆን አገሪቱን ለማመስና ለማፍረስ የማይፈነቅለው ድንጋይ እንደሌለ ተረጋግጧል። ስለሆነም መላ ኢትዮጵያውያንና ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የዚህን አጥፊና አደገኛ ቡድን የጥፋት ዕቅድ በማወቅ በተባበረ ክንድና ቅንጅት ለሽብርተኝነት የማይንበረከክ ስብዕና እንዳላቸው ሊያስመሰክሩና ለሽብርተኞች ትምህርት ሊሰጡ ይገባል!

ኢፕድ

አዲስ ዘመን
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የደም ነጋዴዎችን ሴራ ለማድረቅ

ክብረ ነገስት

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማከተም ወዲህ የዓለምን ሕዝብ ሰላም ከሚፈታተኑ በርካታ ችግሮች መካከል አንዱ የሽብር ሥራ እንደሆነ ማንም ይረደዋል። ሽብር ቤትን ያፈርሳል፤ ጎረቤትን ይበትናል፤ መንግስትን ያስነሳል፤ አገርንም ያጠፋል። እንደውም በአባባሉ ‹‹ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው›› አይደል የሚባለው።

ከሽብር አንጻር በተለይ የውጭ ዓለሙን ትተን በአገራችን ብቻ ያለውን ብንመለከተው በሬ ወለደ አይነት ወሬዎች ብዙ ነገሮቻችንን በእጅጉ እየደበላለቁት መሆኑን መናገር ለቀባሪው አረዱት ነው። አንድ ነገር ብቻ ላንሳ፤ በአሁኑም ሆነ ከዚህ በፊት በነበሩት ጦርነቶች ሳቢያ የሆነውን።

የመጀመሪያው ሽብርን መተዳዳሪያቸው ያደረጉ ኢ-መደበኛ የሚዲያ አካላት ሲሆኑ፤ አሸባሪው ሕወሓት ቀደም ባለው ጊዜ ሆነ አሁን የለኮሰው ጦርነት ከለላ በማድረግ ሽብርና የሽብር ድርጊት ዋነኛ መተዳደሪያቸው አድርገው ሲንቀሳቀሱ ተስተውለዋል፤ ሁለተኛው ደግሞ እራሱ ሕወሓት እና እሱም መሰል አገር ጠል ኃይሎች የሚፈጥሩት ሽብርና የሽብር ተግባሮች ናቸው።

እነዚህ በሕዝብ ስም ሕዝብን የሚሸጡና ኪሳቸውን የሚያደልቡ ኢ-መደበኛ የሚዲያ አካላት የሙያ ስነምግባር ሆነ ሰብአዊ የሞራል እሴት የሌላቸው የመሆናቸው እውነታ የጥፋታቸው አድማስ ከፍ ያለ እንዲሆን አድርጎታል። አገርና ህዝብንም፣ ያስከፈሉትና እያስከፈሉት ያለውም ዋጋ ከፍ ያለ ነው።

ስልጣኑን በህዝባዊ እንቢተኝነት ያጣውና ይህንንም ማመን ያቃተው አሸባሪው ሕወሓትም ቢሆን ስልጣኑን በሽብር መልሶ ለመያዝ በሚያደርገው የአልሞት ባይ ተጋዳይነት መወራጨት በትግራይ ህዝብ ደም እየቆመረ ይገኛል ።

የእነዚህ ታሪካዊ ጠላቶችና የሌላ አካል ተልዕኮ ያነገቡ ኃይሎች እኩይ ተግባር እንደ አገር በተደጋጋሚ ጦርነትና መፈናቀል አምጥቷል። ሕዝባችን የተረጋጋ ሕይወትን እንዳይኖር አድርገውታል። ከእለት ወደ ዕለት እረፍት አልባ ሕይወትን እንዲያሳልፍም ገፋፍተውታል። ሕዝቡን እንዳያመርት አድርገው ተደጓሚና የሰውን ድጋፍ ጠባቂም አድርገውታል። በተለይም አሁን ይህ ባህሪያቸው ተፈጥሯዊ መለያቸው እና ግብራቸው ጭምር መሆኑን አፈትልኮ የወጣው ሰነዳቸው መረዳት ተችሏል።

በሁሉም አካባቢዎች ላይ የእርስ በእርስ ግጭት መፍጠር ከቻሉ በሕዝብ ደም የመቆመሩትን እድል እንደሚፈጥርላቸው፤ ቢዝነሳቸውን በቀላሉ ማሯሯጥም እንደሚያስችላቸው በሰነዳቸው በድፍረት አስቀምጠዋል። ለእነዚህ ኃይሎች ሰላም ገዳያቸው እንጂ አልሚያቸው በፍጹም ሊሆን አይችልም። የእንጀራ ገመዳቸውን ይበጥሰዋል። ለዚህም ነው በቻሉት ልክ ሰላም ማጥፋት ላይ ተሰማርተው የሚንቀሳቀሱት።

እርቅ ከወረደ የለመዱት ጥቅም ይቀርባቸዋል። ከዛም ባለፈ በቀደሙት ጦርነቶች ምን አተረፋችሁልን የሚል ጥያቄ መምጣቱ አይቀርም። ይህንን እውነት ላለመጋፈጥ ሁልጊዜ ጸባ ጫሪነታቸውን ይዘው ይቀጥላሉ፤ እየቀጠሉም ነው። በዚህም ደግሞ ከዓመት በላይ በሆነው ጦርነት ውስጥ እልፍ አላፍ የሆኑ ወገኖቻችን ለእልቂት ተዳርገዋል፤ ጦርነቱን ሸሽት እናቶችና ሕጻናት በየጎዳናው ላይ ወድቀዋል። የሚበሉት አጥተው ተኮራምተዋልም። የሚልሱት የሚቀምሱት በማጣታቸው የተነሳም የሞት አፋፍ ላይ የቆሙት እንዲሁ።

በአፋር በጋሊኮማ፣ በጎንደር በጭና፣ በሰሜን ወሎ አጋምሳ፣ በሰሜን ጎንደር ማይካድራ የተካሀዱ ጭፍጨፋዎች ለዚህ ማሳያ ናቸው። ይህ የታሪክ ጠባሳ የመጣው ከቀደመው ታሪክ መማር ባለመቻላችን እንደሆነ አሁንም ወያኔ እና መሰል የጥፋት ፈረሶች ሊያዩት አይፈልጉም። ከቀደሙ ታሪኮቻችን ከመመርመር ይልቅ የቀደሙ የታሪክ ስህተቶችን ማጉላት ይቀናቸዋል።

ከቀደሙ የታሪክ ስህተቶቻችን ለመማር የሚያስችል እድል እንዳናገኝም አበክረው ይሰራሉ። አንተ የእንትና ዘር፤ አንቺ የእንትና ዘር እየተባባልን በመካከላችን መቃቃር ይፈጥራሉ። ለዚህ ደግሞ ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ረብጣ ዶላሮችን ይቀበላሉ። እርሱን እየተጠቀሙ እኩይ አላማቸውን ያስፈጽማሉ።

አሸባሪው ሕወሓትን እና መሰል የጥፋት ፈረሶችን የሚጋልቡት የውጭ ኃይሎች በእርዳታ እና መሰል ማጭበርበሪያ ስራዎቻቸው ዛሬም ብዙ ተግባርን ይከውናሉ። ዋነኛ ተግባራቸው አድርገውም ይህንን የማጭበርበር ሥራ ይዘውት እየተጓዙ ነው። ይህ በእርዳታ እና መሰል ትርኪ ምርኪ ሥራ የሸፈኑት ተልእኮ ዋነኛ ግቡ አገርን ማፍረስ ነው። ይህንን የታሪካዊ ጠላቶች አገር የማፍረስ አላማ ማከሸፍ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ተቀዳሚ ተግባር ነው።

አገርን ለማዳን ደግሞ ዘር እየቆጠሩ ከመነታረክ መውጣት ያስፈልጋል፤ መተባበር መንፈስን ወደ ውስጥ ማስገባትም ይገባል። በአንድ ላይ እጅ ለጅ ተያይዘን መቆምን መሰረታዊ ግብ ማድረግም የዛሬው ተቀዳሚ ተግባር መሆን ይገባዋል። ይህ ካልሆነ ግን እነኝህ ታሪካዊ የአገራችን ጠላቶች የሚያስነሱት እሳት ሁላችንንም ላንመለስ ለብልቦ እና አቃጥሎ መብላቱ አይቀርም። በተቻለን ሁሉ ከቀደሙ የታሪክ ስህተቶቻችን መማር የአሁን ተግባራችን መሆን አለበት። ምክንያቱም ታሪክ መኖሪያም መማሪያም ነው፤ ታሪክ መሻገሪያም መከበሪያም ነው።

ትርጉሙን ላልተረዳው ታሪክ መጥፎና የማይጠፋ ጠባሳ ነው። ታሪክ ትውልድን እስከነነብሱ መቅበሪያም ነው። አሁን እየሆነ ያለውም ይህ ነው። ስለዚህ ትውልዱን የሚያድን መካሪ አባቶች፣ ምሁራን፣ የፖለቲካ ኃይሎች ያስፈልጉናል። ዘካሪ እና መካሪ እናትና መምህርም ሊኖሩን ይገባል። አንድነት ላይ የሚሰራና ስለአንድነት የሚሰብክ ሕዝብም፣ የፖለቲካ ተዋናዮች መፍጠር ያስፈልጋል።

ጠላት በዋናነት አገርን እያፈረሰ ያለው በሚፈበርካቸው የውሸት ፕሮፓጋንዳዎች ነው። ይህንን ባለፈው ጦርነት ከፍ ያለ ዋጋ ከፍለንበት በአግባቡ መረዳት ችለናል። አሁንም ከትናንቱ ስህተታችን ስለመማራችን በቂ ማስተማመኛ የለም። ዛሬም በጠላቶቻችን ተራ ፕሮፓጋንዳ የሚታለሉ ጥቂቶች አይደለም። ይህ ደግሞ ዳግም የደም ዋጋ እንዳያስከፍለን መስራት ይገባናል።

በጦርነት ቀጠና ያለው ሕዝባችን በወገን ኃይሎች (በመከላከያ ልዩ ኃይል ፋኖና ሚሊሺያ) ሊታመንና ከጎኑ ሊቆም ያስፈልጋል። ጀሮውን ለበሬ ወለደ ትርክት ሰጥቶ ከሀብት ንብረቱ ሊፈናቀል አይገባውም። ጠላቴን እኔ ራሴ ተፋልሜ አቆመዋለሁ ! በሚል ቁርጠኝነት ተነሳስቶ ለጠላቱ ሬት ሊሆን ይገባል።

ሁሉም ለአገሩ ሉአላዊነት መከበር አርበኛ መሆንን ከአሁኑ ጀምሮ ማሳየት አለበት። ጦርነቱ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ስለሆነ እኔን አይነካኝም፤ አይመለከተኝም በሚል መቀመጥ የዋህነት ነው። ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከየአለበት ተሞ በመሄድ ለወገኖቹ መከታ መሆን ይገባዋል። በቻለው ሁሉ ጠላትን ድል ለማድረግ መረባረብ አለበት። አንድ ሆኖ ስለአገር ብሎ መንቀሳቀስም ይገባዋል። ወሬን ሰምተው የተባሉትን ከፍለው የኖሩበትን ቀዬ መልቀቅን ምርጫ ማድረግን ማቆም ያስፈልጋል።

በአምባገነኖች መገዛትና አለመገዛት የሕዝብን ውሳኔ የሚጠይቅ ነው። ይህ እንዳይሆን በነቂስ ወጥቶ መፋለም ምርጫ ሳይሆን ግዴታ እንደሆነ ልናምንበት ያስፈልጋል። እድላችንን በራሳችን ለመወሰን ተግባሩ መፋለም ብቻ መሆንም አለበት። ‹‹ማን ይናገር የነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ›› እንደሚባለው የችግሩን ግዝፈትና ክብደት ከእኛ በቀር ሊያውቀው የሚችል ስለሌለ ሁላችንም ለድሉ ጠጠር መወርወር ላይ መረባረብ አለብን።

ጦርነቱን በአንድነት አለመመከት ቤተሰብን ማጣት፤ ራስን ለአደጋ ማጋለጥና ሕይወትን ጭምር መገበርን ሊያስከትልብን ይችላል። ሁሉም ባለበት ሆኖ የቻለ በጉልበት፤ ያልቻለ ደግሞ በጸሎት ማገዝ ላይ መታተር አለብን። የዚህን ጊዜ አሸናፊነታችንን እናረጋግጣለን። ሰላም ሆነንም ወደልማቱ ጎዳና እንገባለን።

ስናለማና ስንሰራ ደግሞ ጠባችን ይደርቃል፤ መቃቃራችንም ይቀንሳል። ደም በላ ነጋዴዎችም ይከስሙና እድገት ቦታውን ይረከባል። የተረጋጋ ትውልድና አገርም ይኖረናል። ስለሆነም ለአንድነታችን ዘብ እንቁም፤ ለጦራችን ተገንና ብርታት እንሁን በማለት ጽሁፌን ላሳርግ። ሰላም !!

ዜና

# «መስዋዕትነት ከፍለን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በመድረኩ ላይ ንግግር ያደረጉት የሰላም ሚኒስትር አቶ ብናልፍ አንዷለም፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ምንጊዜም ቢሆን ለሰላም በራችን ክፍት ነው ብለዋል። ሆኖም ከሰላም ውጪ በሆነ መንገድ የሀገርን ሉአላዊነት ለሚዳፈሩ፣ እጅ ሊጠመዝዙ ለሚያስቡ እና ሀገር ሊያፈርሱ ለሚመጡ የትኛውንም መስዋዕትነት ከፍለን አደብ እናስገዛለን።

እኛ ኢትዮጵያውያን መስዋዕትነት ከፍለን ሰላም የምናስከብረው ጦረኛ ስለሆንን ሳይሆን ለሰላም የማንከፍለው ዋጋ ስለሌለን ነው ሲሉ ገልፀዋል።

በአሁኑ ጊዜ አሸባሪዎች በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ሰላም በማናጋታቸው ውዱን የሰው ህይወት እያጣን ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ ለዜጎቿ ሰላም በትኩረት ትሠራለች ሲሉ ተናግረዋል።

የኢፌዴሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በበኩላቸው፤ ህፃናት፣ አረጋውያን፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ብቻ ሳይሆኑ መላው ሕዝብ ለመኖር ሰላም እንደሚያስፈልገው በቅርቡ የተከሰቱ የሰላም መናጋቶች ማሳያዎች ናቸው። ስለዚህም ሰላም ከሁሉ ነገር ቀዳሚ መሆኑን አውቀን ሁላችንም ለሰላም ተገቢውን ዋጋ እንድንከፍል እንድንዘጋጅ እላለሁ ብለዋል።

የፍትህ ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ ፍቃዱ ፀጋዬ በበኩላቸው፣ ሰላም ምን ያህል መሠረታዊ እንደሆነ የምናውቀው ሰላም ሲጠፋ መሆኑን በማስታወስ እንደ ህዝብ ጥሩ የሰላም ባህልና ዕሴት ያለን ህዝቦች ነን ብለዋል።

እያንዳንዱ ማህበረሰብ ባለው የአኗኗር ሥርዓት ውስጥ የራሱ የሆነ የሰላም መጠበቂያ ስልቶች አሉት ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ ሆኖም ሰላም በሚናጋበት ጊዜ ኢትዮጵያ ለሰላም ዋጋ ያልከፈለችበት ጊዜ የለም።ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላምን እንዴት ማስከበር እንዳለበት የሚያውቅ ህዝብ ነው የምንለው ሲሉ ገልፀዋል።

ሆኖም ባለፉት ዓመታት በኃይል ታፍነው የነበሩ ችግሮች ባለፉት አራት ዓመታት መለቀቅ ሲጀምሩ በተለያዩ ቦታዎች የሰላም መደፍረስ መከሰቱን ያነሱት አቶ ፍቃዱ፣ በዚህም ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ ህይወት ጨምሮ የአካል ጉዳት እና ውድመቶች ሲያጋጥሙ ቆይተዋል ብለዋል።

ይህ የሰላምን ጠቀሜታ የሚያሳይ አጋጣሚ በመሆኑ ሰላም ሁልጊዜ የምንጠብቀውና የምንንከባከበው ሊሆን ይገባልም ሲሉ አክለዋል።

እንደ አቶ ፈቃዱ ገለፃ፣ በመንግሥት ያለው የሰላም ቁርጠኝነት በተለያዩ አጋጣሚዎች ታይቷል። ለአብነትም ለ20 ዓመታት ሰላምም ጦርነትም ያልሆነውን የኤርትራ እና የኢትዮጵያን ግንኙነት ለመመለስ የሄድንበትን ርቀት ረጅም ቢሆንም ወደ ሰላም መመለስ ችሏል።

እንደማህበረሰብ፣ እንደግለሰብና እንደመንግሥት በሀገር ህልውና እና በህዝቦች ክብር እስካልተመጣ ድረስ ለሰላም የትኛውንም ፍላጎቶቻችንን መተው እንደሚቻልም ከየቱም ነገር በላይ ሰላም ፈላጊ ህዝቦች መሆናችንን አሳይተናልም ብለዋል።

# ዕለቱ አገልጋይነት ፀጋ መሆኑን በሚያሳዩ ተግባራት ይከበራል

**ውብሸት ሰንደቁ**



<u>አዲስ አበባ</u>፡- የአገልጋይነት ቀን አገልጋይነት ፀጋ መሆኑን በሚያሳዩ የተለያዩ ተግባራት እንደሚከናወን የሥራና ክሂሎት ሚኒስትር እና የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በጋራ በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል። ዕለቱን ሚኒስትሮችና ከፍተኛ አመራሮች በየዘርፋቸው ዝቅ ብለው በመሥራት የሌሎችን ጫና በመጋራት እንደሚያሳልፉም ታውቋል።

የአገልጋይነት ቀን ተብሎ የተሰየመውና በዛሬው ዕለት የሚከበረው ቀን አገልጋይነት ፀጋ መሆኑን በሚያሳዩ የተለያዩ ተግባራት የገለፁት ሚኒስትሮቹ፤ ዕለቱን ሚኒስትሮች፣ ከፍተኛ አመራሮች እና በማሕበረሰቡ ከፍተኛ ቦታ የተሰጣቸው ግለሰቦች በየዘርፋቸው ዝቅ ብለው በመሥራት የሌሎችን ጫና በመጋራት ያሳልፋሉ ብለዋል።

የሥራና ክሂሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል በመግለጫቸው፣ አገልጋይነት ሁሉም በየእርከኑ የሚያበረክተው አስተዋፅዖ መሆኑን ጠቁመው የሁሉም የአገልጋይነት መንፈስ የታከለበት አስተዋፅዖ ደግሞ ሀገርን ያቀናል፤ ያፀናልም ሲሉ ገልፀዋል።

የሥራ ትንሽና ትልቅ የሚባል የሌለው በመሆኑ አንድን አገልግሎት የተቃና የሚያደርገው የሁሉም ሥራ ድምር ውጤት ነው ያሉት ሚኒስትሯ፣ በዕለቱ የመንግሥትና የግል ድርጅቶች እና በማኅበረሰብ አደረጃጀት በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች እንደየሙያ መስኩ ዝቅ ብለው አገልግሎት ሲሰጡ ይውላሉ ብለዋል።

ይህ አይዟችሁ ከጎናችሁ ነን ለማለት ከመጥቀሙም ባሻገር በየሥራ መስኩ ያለውን ድካም ለመረዳትና ለመገንዘብ ይረዳል። በባለሥልጣናትና ሥራ ኃላፊዎች ደረጃ ያልተለመዱ አገልግሎት በኃላፊዎች ሲሰጡ የሚውሉ ይሆናል። ይህ ዝቅተኛ የሥራ ቦታ ላይ የሚገኙ ዜጎችን የሥራቸውን ጫና እና ክብደት ለመረዳት ያስችላል ብለዋል።

ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የሥራ ኃላፊዎች የረዳትነትና የሾፌርነት የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ሲሰጡ የሚውሉ ይሆናል ያሉት ወይዘሮ ሙፈሪሃት፣ በተመሳሳይ የሌሎች ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችም እንደየዘርፋቸው አገልግሎት ሲሰጡ ይውላሉ። የፅዳት ዘመቻም አንዱ በዕለቱ የሚከናወን ተግባር ነው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለፃ፣ ከሌሎች ክንውኖች ባሻገር ለሀገር የተዋደቁ፣ ለሰላም ዘብ ቆመው የቆዩ የመከላከያና የፖሊስ አባላት የነበሩና በጡረታ የሚገኙ ዜጎችን ዕውቅና የመስጠት መርሐግብር ይከናወናል።በተጨማሪም ከማኅበረሰቡ በአጋጣሚ የተገኙትን መስፈርትና ምርጫም ሳያስፈልግ እናመሠግናለን ለማለት የተዘጋጀ መርሐግብር አለ።

አገልጋይነት ከእኔ ይጀምራል በሚል መሪ ሃሳብ የሚከናወነው የዕለቱ ዝግጅት በሀገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ መርሐግብሮች እንደሚከበርም ወይዘሮ ሙፍሪሃት ገልፀዋል። በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚከናወኑ መርሐግብሮች አንዱ በተለያየ የሙያ መስክ በሙያቸውና በችሎታቸው ሲያገለግሉ የቆዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን እናመሰግናለን ብለን ዕውቅና የምንሰጥበት ቀን ይሆናልም ብለዋል።

በተመሳሳይ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ደረጃም አበርክቶ ለነበራቸው ዜጎች ምሥጋና የሚቸሩበት ቀን ይሆናል ያሉት ሚኒስትሯ፣ ማመስገን ለቀጣይ የሥራ ተነሳሽነት ትልቅ ትርጉም አለው። ቀጣይነትና ጥራት ያለው ላለው አገልግሎት ትርጉም ይኖረዋል ሲሉ ገልፀዋል።

የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሚኒስትር ዶክተር በለጠ ሞላ በበኩላቸው፣ የጳጉሜ አምሥት ቀናት እያንዳንዱ ቀን ፋይዳ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ታስቦ እንዲውል ተደርጎ እየተከበሩ እንደሚገኙ በመግለፅ፤ ጳጉሜን አራትን የአገልጋይነት ቀን በሚል የምናከብረው አገልጋይነት እንደመንግሥት ተቋም ከእኛ የሚጠበቅ ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ ነው ሲሉ ገልፀዋል።

ቀኑ የሥራ ኃላፊዎች ወደታች ወርደን ለሕዝባችን የምናገለግልበትን ዕድል የሚፈጥር ቀን ይሆናል ያሉት ሚኒስትሩ፣ በተጨማሪም ዲጂታል ሥትራቴጅ ወደታች ወርዶ የሕብረተሰቡን ሕይወት መለወጥ እንዲችል ለማድረግ ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ አሊ በበኩላቸው፣ ከላይ ያለውን ሃሳብ ተጋርተው ለሕዝብ ከሚደረግ አገልግሎት ባለፈ ተጨማሪ የዲጂታል ሥርዓቶች ይፋ እንደሚሆኑ ተናግረዋል።

በፌዴራል ደረጃ ወደ 25 የሚጠጉ ተቋማት አገልግሎቶቻቸውን ወደ ዲጂታል እየቀሩ እንደሚገኙና በዛሬው ዕለትም 319 የሚሆኑ የአገልግሎት መተግበሪያዎች ይፋ እንደሚሆኑ መተግበሪያዎቹም ሰዎች በቤታቸው ሆነው አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችሉ መሆናቸውን ገልፀዋል።

# ትህነግ ሸኔን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አሥረኛው የስለ ኢትዮጵያ መድረክ ላይ እንደገለፁት፤ ትህነግ የራሱን ቅጥረኞች እና የሸኔን አሸባሪዎች በመጠቀም ብሔር ላይ ያነጣጠረ ጥቃት በማድረስ አንዱን ብሔር በሌላው ላይ ለማስነሳት ተደጋጋሚ ሙከራዎችን አካሂዷል። ዋናው የትሕነግ ዓላማ በሀገሪቷ ያሉ ብሔር ብሔረሰቦች ላይ ጥቃት ፈፅሞ ግጭቶች እንዲባባሱ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ሀገር ማፍረስ ነው።

የሽብር ቡድኖች ጥቃቶች ሲያደርሱ አንዱ ብሔር በሌላው ብሔር ላይ የግጭቱ ፈጣሪ አድርገን የምንቆጥር ከሆነ ለሕወሓትና መሰሎቹ ትልቅ ድል ነው ያሉት ኮሚሽነር ጄኔራል፤ እያንዳንዱ ዜጋ ከዚህ ወጥቶ በጋራ በመቆምና ብሔር ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶች ሲፈጠሩ አደጋው የኢትዮጵያውያን አደጋ ነው ብሎ በጋራ መከላከል እንዳለበት አሳስበዋል።

ኮሚሽነር ደመላሽ እንደገለፁት፣ ዛሬ ላይም ትሕነግ የሸኔ የሽብር ቡድንን እንደትልቅ አጋዥ በማሰለፍ በየቦታው ችግር እንዲፈጥሩና አደጋ እንዲያደርሱ የማድረግ ሥራ እየሠራ ነው። በሰሜን ሸዋ አካባቢ የሸኔ የሽብር ቡድን በተለያየ ጊዜ በንፁሐን ላይ ጥቃት ፈፅሟል። የሸኔ ሽብር ቡድን ቀድሞ ሽብርተኛ ብሎ ሲያስረው ሲያሰቃየው የነበረው ትህነግ ጋር እንደገና አብሯል። ትሕነግ የሸኔ አሸባሪ ቡድንን አሁን ዋና የፍላጎቱ ማስፈፀሚያ በማድረግ አደራጅቶ ሥራዎችን የሚያሠራው ኃይል አድርጎታል።

የሽብር ቡድኖቹ በአዲስ አበባም የሽብር ተግባራትን ለመፈፀም ሲንቀሳቀሱ እንደነበር የጠቆሙት ኮሚሽነር ጄኔራል ደመላሽ ነገር ግን መንግሥት፣ የፀጥታ መዋቅሩና ህዝቡ ተረባርቦ በቅንጅት በመስራቱ ተልዕኮአቸው ሊሳካ አልቻለም ብለዋል።

አሁን ላይ የፀጥታና ደህንነት ግብረ ኃይል ውስጥ የፌዴራል ፖሊስ፣ የብሔራዊ መረጃ፣ መከላከያና የተለያዩ አካላት ተመሳሳይ ራዕይ፣ ግብና ዕሴት ይዘው እንደየኦፕሬሽኑ ባህሪ በቅንጅት እየሰሩ እንደሆነ ገልፀዋል።

እነዚህን የሽብር ኃይሎች ባቆየን ቁጥር ጉዳቱ እየጨመረ ይሄዳል ያሉት ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ፣ ሽብርተኞቹን ለማጥፋትና ሕብረተሰቡ በየትኛውም አካባቢ በሰላም ተንቀሳቅሶ የሚሠራበትን ሁኔታ ለመፍጠር እየተሰራ እንደሆነ ገልፀዋል።

የፌዴራል ፖሊስ በአራቱም ማዕዘን በነበሩ የሽብር ጥቃቶች በተለይ ደግሞ ሕብረተሰቡ ላይ በደረሱ ጥቃቶች ሁሉንም የምርመራ ሂደት አጣርቶ ለሕግ ለማቅረብ እየሠራ መሆኑንም ኮሚሽነሩ ገልጸዋል።

ሰሞኑን ከህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ሾልኮ የወጣው ሚስጥራዊ ሰነድ እንዳመለከተው አሸባሪው ህወሓት በኦሮሚያ ውስጥ የሚካሄዱ የልማት ሥራዎችን ለማደናቀፍና ብሄሮችን ለይቶ በማጥቃት የርስ በርስ ግጭት በመፍጠር ሃገርን ለማፍረስ ከሸኔ ጋር በትብብር እየሰራ መሆኑን ማጋለጡ የሚታወስ ነው።

# «በአንድ እጃችን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ጊዜን እየጠበቀ ለተከታታይ ዓመታት ጦርነት ሲከፍት ቆይቷል። በዚህም በወልቃይት ጠገዴ እና አማራ ህዝብ እንዲሁም በኢትዮጵያውያን ላይ በከፍተኛ ደረጃ በደል ፈጽሟል።

ከዚህ ቀደም በነበሩት ጊዜያት የሽብር ቡደኑ በሚፈጥራቸው ጦርነቶች በመስጋት በወልቃይት ጠገዴ አካባቢ የሚኖሩ አርሶ አደሮች በርካታ ለእርሻ ሥራዎች ይውሉ የነበሩ መሬቶቻቸውን ጦም ሲያሳድሩ መቆየታቸውን የተናገረው አቶ ዘነበ ፤ በዘንድሮው ዓመት ግን ቀድመው ተዘጋጅተው ስለነበር በአንድ እጃቸው ክላሽ በሌላ እጃቸው ዶማቸውን ይዘው የግብርና ሥራቸውን ያለምንም መስተጓጎል ማከናወናቸውን ይናገራሉ።

የሽብር ቡድኑ ዋና አለማ አማራን ብሎም ኢትዮጵያውያን ማምረት እንዳይችሉ በማድረግ በኢኮኖሚ ራሷን መደገፍ የማትችል ፣ የተጎሳቆለች ድሃ ኢትዮጵያ እንድትኖር ማድረግ ነው ያለው አቶ ዘነበ፣ በዘንድሮው የመኸር የእርሻ ወቅት ግን በአንድ እጃቸው ክላሽ በሌላ እጃቸው ደግሞ ዶማቸውን ይዘው ሁሉንም አይነት የእርሻ ሥራዎችን በመስራት ወያኔ እና ታሪካዊ የውጭ ጠላቶች ያሴሩትን ሴራ ማክሸፍ መቻሉን ይገልጻል።

እንደ አርሶ አደር ዘነበ ገለጻ ፤ በወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን ከፍተኛ የሆነ የሰሊጥ እና ቦለቄ ምርት ይመረታል። እነኚህ ምርቶች ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ ለሃገሪቱ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ናቸው። ስለሆነም ወያኔ እና አሽከሮቹን በክላሽ ከመፋለም ጎን ለጎን የእርሻ ሥራዎችን በተገቢው መልክ በመስራት የሃገሪቱን ኢኮኖሚ በመደገፍ ጠንካራ ኢኮኖሚ ያላት ሃገር መፍጠር ያስፈልጋል። በኢኮኖሚዋ የጠነከረች ሃገር ከተፈጠረች ደግሞ ደደቢት በረሃ የተፈጠረውን የከፋት ቡድን እዚያው በተፈጠረበት ቦታ መቅብር ይቻላል። በዚህም የታሪካዊ ጠላቶቻችን ህልም ቅዥት ማድረግ ይቻላል።

ሌላኛዋ የወልቃይት ጠገዴ አዲ ፍልሆ ቀበሌ ነዋሪ እና የአርሶ አደር ሚሊሻ የሆነችው ረድኤት ጎይም እንደገለጸችው፤ ህወሓት ከ40 ዓመት በላይ የወልቃይት ጠገዴን ህዝብ ሲያስተዳድር በነበረበት ጊዜ በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ላይ ያልፈጸማቸው ግፎች አልነበረም። ሲፈጠር ጀምሮ ጥፋት መታወቂያው የሆነው የህወሓት የሽብር ቡድኑ በስልጣን ዘመኑ በወልቃይት ጠገዴ ብሎም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በሰራቸው ግፎች ከመጸጸት ይልቅ አሁንም የወልቃይት ጠገዴ እና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ አርሶ እና አምርቶ እንዳይበላ በማሰብ የክረምቱን ወቅት እየጠበቀ ወረራ በመፈጸም የእርሻ ሥራዎችን እያስተጓጎለ በአማራ እና በኢትዮጵያውያን ላይ ርሃብ እንዲኖር ከፍተኛ ሥራ ሰርቷል።

“ከዚህ ቀደም በነበሩት የክረምት ወቅቶች አማራ ማምረት እንዳይችል አድርጓል። በጦርነት ውስጥ የአመረቱትንም በከባድ መሳሪያ በመደብደብ አቃጥሏል። በዘንድሮው ክረምት ግን የወልቃይ ጠገዴ ህዝብና መላው ኢትዮጵያዊ ተዘጋጅቶ ስለነበር የወያኔን የጥፋት ሥራዎች ማክሸፍ ተችሏል” ያለችው ረድኤት ፤ በዚህም መላው የወልቃይት ጠገዴ ማሳዎች በዘር መሸፈኑን ትናገራለች።

የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በአንድ እጁ በዘር የተሸፈኑትን ማሳዎች በተገቢው መልኩ እያረመ እና እየኮተኮተ ነው። በሌላ እጁ ደግሞ አካባቢውን ከወራሪው ቡድን ለመከላከል መሳሪያ አንግቦ እየታገለ ነው ስትልም ገልጻለች።

ሌላው የወልቃይት ጠገዴ ነዋሪ የሆኑት አርሶአደር እና ሚሊሻ ጎሹ ቱኩ በበኩላቸው፣ የሽብር ቡድኑ ህወሓት በዘንድሮው ዓመትም እንደዚህ ቀደሙ የወልቃይት ጠገዴን የእርሻ ማሳ በዘር እንዳይሸፈን ለማድረግ ጥረት አድርጎ ነበር። ይሁን እንጂ የወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ የአርሶ አደር ሚሊሻ በአንድ እጁ መሳሪያ በሌላ እጁ ማጭድ በመያዝ የእርሻ ሥራውን ያለምንም መስተጓጎል እየሰራ ነው። በዚህም የሽብር ቡድኑን ቅዠት ማክሸፍ ተችሏል።

ሰሞኑን ከአሸባሪው ህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ሾልኮ የወጣው ሚስጥራዊ ሰነድ የአማራ አርሶ አደር የእርሻ ሥራውን እንዳያከናውን እና ያረሰውን እንዳይሰበስብ በማድረግ ልማቱን ማደናቀፍ እንዲሁም ሰርጎገቦችን በማስገባት ህብረተሰቡን ማሸበር እንደ ስልት አቅዶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ማጋለጡ ይታወሳል።

# አገልጋይነት

አገልጋይነት በብዙ መልኩ ይገለፃል። አገልጋይነትና ቅንነት፤ አገልጋይነትና ታማኝነት፤ አገልጋይነትና አርአያነት ወዘተርፈ የሚለያዩ ባህርያትና ተግባራት አሉት። ከአገልጋይነት ጋር በተያያዘ ብዙ ማለት የሚቻል ሲሆን፤ ከወቅታዊነቱና ከአገራዊ አቅጣጫነቱ አኳያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ስለ አገልጋይነት ከሰጡት ብያኔና ማብራሪያ እንጀምር።

እንደ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ አስተያየት "አገልጋይነት ታላቅነት ነው። ክብር የሚገኘው ከማገልገል ነው። ፈጣሪን፣ አገርን፣ ሕዝብን፣ ከማገልገል ውጭ ምን ሕይወት አለ። ሁላችንም በአንድ ቦታ አገልጋዮች በሌላም ቦታ ተገልጋዮች ነን። አገልጋይነት የሁላችንም ባህልና ሥነ ምግባር ከሆነ የትኛውም መ/ቤት መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ይሆናል። የሆኑ አካላት ብቻ እንዲያገለግሉን ከጠበቅን ግን በአንዳንድ ቦታዎች ተፈልጎ የሚገኝ ብርቅ ሀብት ይሆንብናል። በቂና ብቁ አገልጋዮች የሌሏት አገር፣ በዕድገት መራቅና መምጠቅ ይቸግራታል።"

"አገልጋይነት የሁላችንም ባህልና ሥነ ምግባር ከሆነ የትኛውም መስሪያ ቤት መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ይሆናል።" በማለት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መግለፃቸውም እንዲሁ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

ሆኖም የሆኑ አካላት ብቻ እንዲያገለግሉን ከጠበቅን አገልጋይነት በአንዳንድ ቦታዎች ተፈልጎ የሚገኝ ብርቅ ሀብት ይሆንብናል። በቂና ብቁ አገልጋዮች የሌሏት አገር፣ በዕድገት መራቅና መምጠቅ ይቸግራታል።" ያሉትም እንዲሁ።

ጉዳዩ መሰረታዊ ነውና ከሀይማኖት አስተምህሮ አኳያም ብናየው ጉዳዩ ሩቅ አይደለም። አንድ ምሳሌ ወስደን እንመልከት።

በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ዕርሻ፡ ቍፋሮ፤ ማንኛውም ሥጋዊና መንፈሳዊ የማገልገል ሥራ፤ ዕንጨት መስበር፡ ውሃ መቅዳት፡ እንጀራ መጋገር፡ ወጥ መቀቀል፡ ጠላ መጥመቅ፡ ሰፌት መስፋት፤ ቅዳሴ፡ ውዳሴ፤ የመሰለው ኹሉ (2ዜና 8፡14) የአገልግሎት ተግባራት መሆናቸው ተዘርዝሮ ይገኛል። ከዚህ አኳያ የአገልግሎት ወሰን ምን ያህል ሰፊ እንደ ሆነ የምንገነዘብ ሲሆን፤ በሌሎች ሀይማኖቶችም ከዚህ የሰፋ ቢሆን እንጂ አንሶ የሚገኝ አይመስልም።

አገልጋይነትን ከጊዜና ቦታ አኳያም ማየት ይቻላል።

አገልጋይነት በጊዜና በቦታ የመወሰኑ ጉዳይና ከዛውም ጋር ተያይዞ የመታወሱ፤ የመዘከሩ ጉዳይ ሲሆን፤ ይህም "የካቲት ወር የአፍሪካውያን ወር ይባላል፡፡ ይህን ወር የአፍሪካውያን ወር ያሰኘው ብቸኛ ምክንያት የዓድዋ ድል ነው፡፡ ነጮች አፍሪካውያንን በግፍ በሚረግጡበት፣ በባርነት በሚገዙበት፣ ያሻቸውን ያለከልካይ በሚፈፅሙበት በዚያን ወቅት "እምቢኝ! አገሬን በቅኝ አላስገዛም" ብሎ በጀግንነት የተነሳ፣ ተነስቶም የቅኝ ገዢዎችን በትር በሀይል መስበር የተቻለበት ወር ይህ የካቲት ወር ነው፡፡" ከሚለው ክፍለ ዘመን የተሻገረና ከአገርም አልፎ አህጉርን ያጠቃለለው ድል ነው።

ለማንም ግልፅ በሆነ መልኩ ይህ ድል ባለቤት አለው። ባለቤቶቹም ባለ ድሎቹ ናቸው። የዛሬውን ቀን አስመልክተን እየተነጋገርነው ባለው "የአገልግሎት ቀን" መሰረት ደግሞ ለዚህ ሁሉ ድል የበቁትና እኛንም ለዛሬው ቀን ያበቁን አያት ቅድመ አያቶቻችን ጀግኖች ብቻ ሳይሆኑ፤ አገልጋዮቻችንም ናቸው ማለት ነውና ዛሬም፣ በዚህ የአገልጋይነት ቀን ሊታወሱና ሊዘከሩ ይገባል ማለት ነው።

ከዚሁ ጋር አብሮ ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ የእቴጌይቱ ተግባር ነው። እቴጌ ጣይቱ ለፋሽስቱ ‹‹የዛሬ ሳምንት አድርገው፡፡ እኔ ሴት ነኝ፡፡ ጦርነት አልወድም፤ ነገር ግን አገሬን እንደዚህ ያለ ክብር የሚነካ ዘለፋ ከምትሸከም ጦርነትን እመርጣለሁ፡፡ ሂድ መንገዱን ጨርቅ ያድርግልህ! እግሩን ለጠጠር ደረቱን ለጦር አስጥቶ ደሙን ለአገሩ ፍቅር አፍስሶ ለአፈሩ ክብር ለብሶ እሱ ወድቆ አገሩን የማያቆም እዚህ ያለ እንዳይመስልህ! ሂድ! የኢትዮጲያን ሰው ባታውቀው ነው፡፡ ለአገሩ መሞት ማለት ለሀበሻ ጌጡ ነው፡፡ ሂድ ባሻህ ግዜ ተመለስ ተሰናድተን እንጠብቅሃለን፡፡ ያንተን ወንድነትና የጣይቱን ሴትነትም ያን ግዜ




እናየዋለን ሂድ መንገዱን ጨርቅ ያድርግልህ፡፡›› ነበር ያሉት። በቂና ብቁ አገልጋዮች የሌሏት አገር እንደ አገር መቀጠል ይከብዳታል፡፡ አገልጋዮች ያሏት አገር ደግሞ ከራሷ አልፎ ለሌሎችም መከታ ትሆናለች፡፡ ለዚህ ደግሞ የአድዋ ጀግኖች ከጀግነነትም አልፈው አገልጋይም እንደነበሩ አመላካች ነው፡፡ በሌላ ጎኑ እቴጌ ጣይቱ ታላቅ የጦር መሪ ብቻ ሳይሆኑ ብቁ የኢትዮጵያና ህዝቦቿ አገልጋይ ነበሩ እያልን ነው። ወደ ዘመናዊው ቢሮክራሲ እንምጣ።

በአሁኑ ዘመን ቢሮክራሲ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው በየደረጃው ባሉ የስራ ሃላፊዎች ዘንድ ስልጣንን ለግል ጥቅም የማዋል የሌብነት አመለካከትና ድርጊት መስፋፋት፤ እንዲሁም የመልካም አስተዳደር መጓደል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ሄዶ የስልጣን ባለቤት የሆነውን ህዝብ ማስቆጣት ነበር። በቅድመ ዐቢይ የህዝብ ተቃውሞዎች ውስጥ ሲታይ የነበረው ይኸው አይነት የማጋለጥ እንቅስቃሴ እንደ ነበር ይታወሳል። በሃገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የተቀሰቀሰው ተቃውሞ መሰረታዊ ምክንያትም በየደረጃው የአገልጋይነት ስሜት መጥፋት የፈጠረው መሆኑ አይዘነጋም።

ይህን በወቅቱ በነበሩት የመንግስት ባለስልጣኖች ዘንድ የጠፋው የህዝብ አገልጋይነት ተግባር መጓደል የነበረውን መንግስት ወደ ደርዝ እንዲገፋ ምክንያት ሆኖ እንደ ነበር ማንም ያውቃል። የወቅቱ መንግስትና ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግም በሚገባ ተረድተውታል። ህዝብ በውክልና ስልጣን ሲሰጣቸው የጣለባቸውን አደራ መወጣት እንዳልቻሉም ተገንዝበዋል። እናም የህዝብ አገልጋይነት ጉድለቱን ለማስተካከል ቃል ገብተው እርምጃ ለመውሰድ ቢሞክሩም መሽቶ ነበርና አልተሳካም። በመጨረሻም ስርዓቱ ተንኮታኩቶ ወደቀ፡፡

ይህ የሚያሳየን፣ ወይም ከነበረው አጠቃላይ ሁኔታ የምንረዳው በተለያየ ደረጃ ሃላፊነት የተሰጣቸው ግለሰቦች ወይም ባለስልጣኖች የህዝብ አገልጋይነት አመለካከት እንዲኖራቸው በቅድሚያ ስልጣናቸው አገልግሎት ፍለጋ ወደ መስሪያ ቤታቸውና ቢሯቸው በሚመጡ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት በሚፈልጉና በሚጠይቁ ሁሉም ዜጎች በውክልና የተሰጠ መሆኑን መገንዘብ ያለባቸውና በዛው ልክም ማገልገል ያለባቸው መሆኑን ነው። ካልሆነ ያው ከላይ እንደተባለው ተንኮታኩቶ መውደቅ ይመጣል ማለት ነው።

ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ሲሉ እንደ ሚሰማው የህዝብ አገልጋይነት ‘ሀ’ ‘ሁ’ የሚጀምረው ሀላፊነትን ከማወቅና ውክልናን በአግባቡ ከመረዳት ነው። ይህ ከታወቀ አገልጋይነት ከባድ አይሆንም።

በዚህ ብቻም አይወሰንም። ተገልጋይ የአገልጋይን ተገቢ አገልግሎት ማወቅ ይጠበቅበታል። በማያውቀው አይፈርድምና የሚያውቅበት መንገድ ሊኖር የግድ ይሆናል። ይህ ማለት ከዚህ ባሻገር ህዝብ በውክልና ስልጣን ላይ ያስቀመጠውን አካል የሚከታተልበት፣ የሚያርምበትና ውክልናውን የሚያነሳበት ስርአት ሊኖር ይገባል ማለት ይሆናልና ይህም ሊታሰብበት ይገባል እያልን ነው። ይህንን ትንሽ ሰፋ አድርገን ማየት ይኖርብን ይሆናል።

በየሰነዱ ላይ ሰፍሮ እንደሚነበበው፣ የሚመለ ከታቸውም ሲናገሩ እንደሚሰማ በዴሞክራሲያዊ ስርአት የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ህዝብን በአግባቡ እንዲያገለግሉ ቁጥጥር ማድረግና ማረም የሚያስችሉ ስርአቶች አሉ። አንደኛው ሃሳብን የመግለጽ ነጻነትና ይህ መብት እውን የሚሆንበት የፕሬስ ነጻነት መረጋገጥ ነው። ፕሬስ የመንግስት አሰራር ላይ ያሉ ድክመቶችን በማጋለጥ እንዲሁም የህዝብን ፍላጎት ለመንግስት በማሳወቅ የህዝብ ድምጽ ሆኖ ያገለግላል። በሌላ በኩል የመንግስትን ክንውንን ለህዝብ ይገልጻል። የፕሬስ ነጻነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የመንግስትን የህዝብ አገልጋይነት መቆጣጠርና ማረም አይቻልም። የመንግስት የህዝብ አገልጋይነት የፕሬስ ነጻነት ባደገበት ልክ ይወሰናል። እናም የመንግስትን የህዝብ አገልጋይነት ለማጎልበት በሀላፊነት የሚመራ ነጻ ፕሬስን ማጎልበት አማራጭ የለውም። የሲቪክ ማህበራትንም ከዚሁ ጋር አያይዞ ማሰብ ያስፈልጋል።

ሌላው አገልጋይነት የሚጠቀስበት መንገድ ከላይ ካለነው ትንሽ ወጣ ያለ ሲሆን፤ እሱም የህዝብን ጥቅም ለተወሰነ ቡድን ወይም ቡድን አባላት አሳልፎ ከመስጠት ጋር የተያያዘ ነው። ለለምሳሌ ያህልም ከአንድ ፅሁፍ ውስጥ የተወሰደን፤ ይህንን አንቀፅ እንመልከት። "አገልጋይነት …"፣ "መገልገያነት …" እና የመሳሰሉትን ቃላት ልብ እንበል።

በጥቅሉ ከ2008 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ ህዝባዊ አመፅና ተቃውሞ በመላ አገሪቱ ተስፋፋ። ከ2009 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ ደግሞ ኦህዴድ እና ብአዴን በኦሮማራ ጥምረት አማካኝነት ራሳቸውን ከሕወሓት አገልጋይነት ነፃ አወጡ። በ2010 አጋማሽ ላይ የሕወሓት የስልጣን የበላይነት ተወግዶ አዲስ አመራር ወደ ስልጣን መጣ። አዲሱ አመራር ወደ ስልጣን ከመጣበት ግዜ ጀምሮ እስከ 2011 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ አምስቱን አጋር ድርጅቶች እና ደህዴንን ከሕወሓት ተፅዕኖ እና መገልገያነት ነፃ አወጣ። በዚህ ረገድ የአብዲ ኢሌ ከስልጣን መወገድ፣ እንዲሁም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ሀረሪ፣ አፋርና ድሬዳዋ የተደረጉት የአመራር ለውጦች ይጠቀሳሉ።

በወቅቱ ተፅፎ ከነበረ ፅሁፍ ቆንጥረን እዚህ ያመጣነው አንቀፅ እንደሚያሳየው ቅድመ ዐቢይ አስተዳደር አይደለም የአገልጋይነት ፍላጎትና ተግባር ሊኖረው ቀርቶ መንፈሱ እንኳን እንዳልነበረው ያሳያል። በዚሁ ምክንያትም ውጤቱ ሊገለገል የሚገባው ህዝብ አለመገልገሉ በፈጠረበት ተቃውሞ መንበሩን ነቀነቀው፤ ነቅንቆም ጣለው።

ሌላው ከአገልጋይነት አኳያ ብዙ ጊዜ ፀያፍ የሚሆነው፣ ቢሮክራሲው ህዝብን በማገልገል ፋንታ ህዝብ እሱን እንዲያገለግለው የመፈለጉ ጉዳይ ነው። ለዛ ማሳያ ይሆነን ዘንድ እሩቅ ሳንሄድ አሁንም ቅድመ ዐቢይ አሕመድ አስተዳደርን ማየት እንችላለን።

በቅድመ ዐቢይ አስተዳደር ወቅት ጮክ ብለው ይሰሙ ከነበሩት ድምፆች መካከል “በአብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚመራ ኢህአዴግ ከሌለ ኢትዮጵያ እንደ አገር ትፈርሳለች፣ ህዝቦቿን በጦርነት ያልቃሉ”፤ “እኔ ከሌለሁ አንተ አትኖርም”፤ “… በኢህአዴግ መቃብር ላይ ነው” የሚሉትና የመሳሰሉት ነበሩ። እነዚህ ደግሞ በምንም መልኩ ህዝብን የማገልገል፤ ህዝብን የማዳመጥ፤ ህዝብን የማሳተፍ ወዘተርፈ ተግባራት አይደሉምና በወቅቱ አገልጋይነት አለ ለማለት ያስቸግራል። (ካስፈለገ እነዚህን ሰፋ አድርጎ ወደፊት በሌላ ፅሁፍ በተንተን አድርጎ በማሳየት ምን ያህል "አገልጋይ" ሳይሆኑ "አግላይ" እንደ ነበሩ ማሳየት ይቻላል። በተለይም ከ"ወካይ"፣ "ተወካይ"፤ "መራጭ" "ተመራጭ … አኳያ ብዙ የሚያወያዩ፣ የሚያነጋግሩ ከመሆናቸው አንጻር)

ባጠቃላይ፣ "አገልጋይነት ታላቅነት ነው። ክብር የሚገኘው ከማገልገል ነው። ፈጣሪን፣ አገርን፣ ሕዝብን፣ ከማገልገል ውጭ ምን ሕይወት አለ። ሁላችንም በአንድ ቦታ አገልጋዮች በሌላም ቦታ ተገልጋዮች ነን። አገልጋይነት የሁላችንም ባህልና ሥነ ምግባር ከሆነ የትኛውም መ/ቤት መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ይሆናል። የሆኑ አካላት ብቻ እንዲያገለግሉን ከጠበቅን ግን በአንዳንድ ቦታዎች ተፈልጎ የሚገኝ ብርቅ ሀብት ይሆንብናል። በቂና ብቁ አገልጋዮች የሌሏት አገር፣ በዕድገት መራቅና መምጠቅ ይቸግራታል።" ያሉትን እዚህ መድገሙ አስፈላጊ ነውና በዚሁ እንሰናበት።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# አገልጋይነት በወጣቶች አንደበት

አስናቀ ፀጋዬ

ነፃ አገልግሎት ሰዎች ገንዘብ ወይም ሌላ የተለየ ጥቅም ሳይፈልጉ በራሳቸው ተነሳሽነት ወደውና ፈቅደው የሚከውኑት ተግባር ነው። በነፃ አገልግሎት ሰዎች ጉልበታቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ግዜያቸውን ወይም እጃቸው ላይ ያለውን ሀብት ለሌላቸው ያበረክታሉ። ይህም በበጎ የሚታይና በአርያነት የሚጠቀስ ተግባር ሲሆን በዚሁ ነፃ አገልግሎት በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሲሆኑ ይታያል።

የነፃ አገልግሎት ተግባር እንዲቃናና በርካቶችም በዚህ በጎ ተግባር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ወጣቶች ቁልፍ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ። በዚህ የክረምት ወቅትም በርካታ ወጣቶች በተለያዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ውስጥ በመሳተፍ እውቀታቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ግዚያቸውንና ገንዘባቸውን አገልግለቱን ለሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች በነፃ እየሰጡ ነው። በዚሁ ተግባር አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ ወጣቶችን መጥቀስም ይቻላል።

ወጣት ብርሃኑ ጋሻው የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ነዋሪ ነው። በክፍለ ከተማው የወጣቶች ማህበር ሰብሳቢም ነው። የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን ገና በልጅነቱ በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ እንደጀመረ ይናገራል። አሁንም በዚሁ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ ሙሉ ግዜውን በመስጠት እየሰራ እንደሚገኝ ይገልፃል።

እርሱና ሌሎች ወጣት ጓ ደኞቹ በዚህ የክረምት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች በጎነት በሆስፒታል፣ በአይሲቲና የመአድ ማጋራት መርሃ ግብሮች ላይ እየተሳተፉ እንደሚገኙ ያስረዳል።

በተለይ በጎነት በሆስፒታል በሚለው መርሃ ግብር ከክፍለ አገር ወደ ሆስፒታል የሚመጡ ታካሚዎችን መረጃ በመስጠት፣ ቋንቋ በማስተርጎምና በከተማዋ ሲንቀሳቀሱ የሚፈልጓቸውን ቦታዎች በማሳየት የነፃ አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱን ይጠቁማል። ታካሚዎችን የማስታመምና የማገዝ ስራዎችን ሲሰራ መቆየቱንም ይናገራል።

በአነስተኛና ጥቃቅን ስራ ተሰማርቶ እንደሚገኝ የሚናገረው ወጣት ብርሃኑ የነፃ በጎ ፍቃድ አገልግሎቱን ከስራው ጎን ለጎን እንደሚያከናውን ይገልፃል። የነፃ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በመስጠቱ ከፍተኛ የአእምሮ እርካታ እንደሚሰማውና ‹‹በጎ ስራ መስራትና የወለደን ማህበረሰብ ማገለግል ግዴታም ውዴታም ነው›› ይላል።


‹‹አገልጋይነት ከወጡበት ማህበረሰብ ዝቅ ብሎ ማገዝ ነው›› የሚለው ወጣት ብርሃኑ በተለይ አቅመ ደካሞችን መርዳት ትልቅ የመንፈስ እርካታ እንደሚሰማው ይገልፃል። በነፃ አገልግሎ ከአባቶችና እናቶች የሚያገኘው ምርቃት ለእርሱ ከገንዘብ በላይ መሆኑንም ያመለክታል።

ሌሎች ወጣቶችም የአገልጋይነት መንፈስ ተላብሰው ወገኖቻቸውን እንዲያገለግሉና የወጡበትን ማህበረሰብ እንዲረዱ ካልባሌ ቦታ ርቀው ወደዚህ የተቀደሰ ተግባር እንዲመጡ ጥሪውን ያቀርባል። ይህም ለቀጣይ ህይታቸው መቃናትና የስራ ልምድና ተነሳሽነት እንዲያገኙ አስተዋፅኦ እንዳለውም ይጠቅሳል።

በጎ ፍቃደኝነት እድሜ፣ ፆታ፣ ሃይማኖትና ብሄር የማይለይ በመሆኑ ሁሉም ወጣቶች የአገልጋይነት ስሜት ተላብሰው በበጎ ፍቃድ ቢሳተፍ አገልግሎቱን ለሚፈልጉ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ መሆን እንደሚቻልም ነው ወጣት ብርሃኑ የሚገልፀው።



ወጣት ፀሃይ ተሾመ፤



ወጣት ዚያዳ ያጅቡ፤

ወጣት ዚያዳ ያጅቡ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ አምስት ነዋሪ ናት። የነፃ የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን ገና የሰባት ዓመት ልጅ እያለች በትምህርት ቤት እንደጀመረችና በሂደት እያሳደገችው እንደመጣች ትናገራለች። አገልግሎቱን ስትጀምር በአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ውስጥ በመታቀፍ ህፃናቶችን በማስጠናት እንደነበርም ታስታውሳለች።

በዚህ መልኩ የጀመረችው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እያደገ፤ በኮቪድ ወቅትም ጎልብቶ ዛሬ ላይ የትራፊክ ነፃ አገልግሎት እየሰጠች እንደምትገኝ ትገልፃለች። ‹‹ነፃ የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን ለመግለፅ ቃላቶች ያጥሩኛል›› የምትለው ወጣት ዚያዳ በህይወቴ ከሚያስደስቱኝ ስራዎች መካከል አንዱ ይኸው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ነው ትላለች። በህይወት ዘመኗ ደስ ብሏት እየሰራችው ያለችው ስራም የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መሆኑን ጥገልፃለች። ከዚሁ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ስራዋ በተጨማሪ ትምህርት እንደምትማርና ማታ ላይ እንደምታስተምርም ነው ወጣት ዚያዳ የምትናገረው።

ሁሉም ወጣቶች የአገልጋይነትን መንፈስ በመላበስ በበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ላይ መሳተፍና ህብረተሰቡን ማገዝ እንደሚችሉ የምትናገረው ወጣት ዚያዳ፤ ሰው ለመርዳት በገንዘብ ብቻ ሳይሆን በእውቀትና በጉልበት መርዳት ስለሚቻል ሁሉም ወጣት ለማገዝ ፍቃደኛ ከሆነና ውስጡን ለበጎ ስራ ዝግጁ ካደረገ በርካታ ስራዎችን መስራት እንደሚቻል ታብራራለች።

ወጣቱ በህይወት ዘመኑ በጎ ስራ ሰርቶ ማለፍ ስላለበት ከሚሰሩት ስራ ጎን ለጎን እርዳታ የሚሹ ወገኖችን በመጠየቅና በማገዝ በርካታ ስራዎችን መስራት እንደሚችሉም ትጠቁማለች። ይህም ከምንም በላይ የአእምሮ እርካታን እንደሚሰጣቸው ትገልፃለች።

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሁለት ወጣት ማህበር በአስተባባሪነት እየሰራ የሚገኘው ወጣት አቤል ባደገ ከማስተባበር ስራው በዘለለ በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሃግብር በቤት እድሳት፣ በሆስፒታል አገልግሎት፣ አረጋውያንና የጎዳና ልጆችን በማንሳትና በመመገብ፣ የበጎ ፍቃድ ትምህርት በመስጠት ስራ በተዘዋዋሪ ሲሳተፍ እንደቆየ ይናገራል።

‹‹የሰው ልጅ የተፈጠረው ለአንድ አላማ ነው ያም ማገልገል ነው›› የሚለው ወጣት አቤል መገልገለው የሚጀምረውም ከሰብአዊነት ነው ይላል። በተለይ ወጣት ከማንም በላይ ጉልበትና ግዜ ያለው በመሆኑ ይህን ጉልበቱንና ግዜውን ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ ማበርከት እንደሚገባው ያመለክታል። ከእርሱ በታች ያሉ ታናናሾቹን ደግሞ ስለዚህ አገልግሎት ማስተማር እንደሚገባውም ይጠቅሳል።

በበጎ ፍቃድ አገልግሎት በመሳተፍ ስምንት ዓመት እንዳስቆጠረና በነፃ አገልግሎት ሲሰጥ ደስ እንደሚለው፤ ይህን አገልግሎት ክረምት ወይም በጋ ሳይል እንደሚሰጥ ያስረዳል። በዚህ አገልግሎት የአእምሮ እርካታ ለማግኘት ምንም ነገር ከማድረግ የሚያግደው ነገር እንደሌለም ይናገራል። ሙሉ ግዜውን ለበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሰጠ ቢሆንም አሁንም ብዙ እንዳላገለገለ እንደሚሰማውም ይገልፃል።

ተፈጥሮ የራሷ ህጎች አሏት። ከነዚህ ህጎች ውስጥም አንዱ የመስጠትና የመቀበል ህግ እንደሆነ የሚገልፀው ወጣት አቤል፤ አንድ ሰው ወደዚህ ምድር የመጣው ለመስጠትና ለመቀበል እንደሆነ ያስረዳል። የሰው ልጅ በህይወቱ መልካም ነገርን ማግኘት ከሆነ መልካም ነገርን መስጠት እንዳለበት ይገልፃል።

እርሱም በህይወቱ ስኬትና የተሻለ ነገር ስለሚፈልግ ለሌሎች የተሻለ ነገር በመስጠት ማግኘት እንደሚችል አምኖበት ወደ በጎ ፍቃድ አገልግሎት እንደገባ ያመለክታል። ቋሚ የሚለው ገቢ እንደሌለውና ሙሉ ግዜውንም ለዚሁ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንደሰጠ ይጠቁማል።

በጎ ፍቃድ አገልግሎቱ ላይ ብቻ አተኩሮ በመስራቱ ከተለያዩ ሱሶች ስለመራቁ፣ ስራ አጥ መሆኑን ስለመርሳቱ፣ ለነገ የተሻሉ ተስፋዎችንና መንገዶችን ለማየት ስለመቻሉም ነው ወጣት አቤል የሚገልፀው።

ወጣቱ በዚህ ግዜ አስተሳሰቡን ቀይሮ የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን መስጠት እንዳለበትም ተናግሮ፤ ወደኋላ ከሚጎትቱ ነገሮች በመላቀቅ በነፃ ማገልገልን መማር እንዳለበትም ይመክራል። በዚህም ያተርፋል እንጂ አይከስርም ይላል።

ወጣት ፀሃይ ተሾመ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወጣቶች ማህበር ውስጥ ምክትል ሰብሳቢ ሆና ትሰራለች። በሁሉም የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዘርፎች ውስጥ ወጣቱ ተሳታፊ ሆኖ እንዲሰራ የማስተባበር ስራዎችን እንደምትሰራም ትናገራለች። እርሷም በዚሁ የበጎ ፍቃድ ስራ ተሳታፊ ሆና እየሰራች እንደምትገኝም ትገልፃለች።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን ከአስር ዓመት በፊት እንደጀመረች የምትናገረው ወጣት ፀሃይ፤ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ውስጥ መሳተፍ ከሁሉም በላይ ትልቅ የአእምሮ እርካታ እንደሚሰጣት ትገልፃለች። ለነገ ህይወቷ ትልቅ መሰረት እንደሆናትም ትናገራለች። ‹‹ገንዘብና ሀብት አላቂ ቢሆንም የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ግን እርካታን የሚያጎናፅፍ በመሆኑ መቼም የሚያልቅ አይደለም›› ትላለች ወጣት ፀሃይ።

እርሷ በምታስተባብረው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ወጣቶች በሁሉም ዘርፎች ስራዎችን ሲሰሩ እንደቆዩ ተናግራ፤ በተለይ በበጎነት በሆስፒታል፣ በቤት እድሳት፣ አቅመ ደካማዎችንና አካል ጉዳተኞችን በመደገፍ፣ ህፃናትን በመደገፍ በማስተማርና በትራፊክ አገልግሎት በርካታ ስራዎች እንደተከናወኑ ታብራራለች።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በሚፈለገው ልክ ተደራሽ አልሆነም የምትለው ወጣት ፀሃይ፤ በተለይ ወጣቱ በንቃት እየተሳተፈ ባለመሆኑ አቅመ ደካሞችንና በገቢ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማገዝ እንደሚጠበቅባቸው ትጠቁማለች። ይህ ደግሞ ከዛሬ ሊጀምር ይገባል ትላለች።

ወጣቱ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት መሳተፍ ካልቻለና ለወጣበት ማህበረሰብ ርዳታና ድጋፍ ካላደረገ ጨካኝ፣ የማይተጋገዝ፣ የማይረዳዳና የማይተጋገዝ ማህበረሰብ እንደሚፈጠርም ነው ወጣት ፀሃይ ስጋቷን የምትገልፀው። በወጣቱ በኩልም ከበጎ ፍቃድ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ያለው ግንዛቤም አነስተኛ በመሆኑ በዚህ ረገድ ጠንካራ ስራ ሊሰራ እንደሚገባም ታሳስባለች።

ከበጎ ፍቃድ አገልግሎት ውጪ ቋሚ ስራ እንደሌላት የምትናገረው ወጣት ፀሃይ፤ ሙሉ ግዜዋን በዚሁ የነፃ በጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ አተኩራ እየሰራች እንደምትገኝ ትገልፃላች። ወጣቱ ማህበረሰብ ባለው ሞያና እውቀት ክፍያ ሳይጠብቅ በአገልጋይነት መንፈስ ህብረተሰቡን በነፃ እንዲያግዝ መልእክቷን ታስተላልፋለች።

ይህን ለማድረግ ታዲያ በቅድሚያ በወጣቱ በኩል የአስተሳሰብ ለውጥ ሊኖር ይገባል ትላለች። በጎነት ክፍያው ለራስ በመሆኑ ሁሉም በበጎነት ስራዎች ውስጥ እስከተሳተፈ ድረስ ሌሎችን ጠቅሞ ወደፊት ራሱንም መጥቀም እንደሚችል አውቆ መስራት እንዳለበትም ትመክራለች።

# የምድር በረከት

## የማዕድን ዘርፉ እየተጠናቀቀ ባለው የ2014 ዓመት

**ስምስም ምንግሥቱ**

የኢትዮጵያ መንግስት በአስር ዓመቱ የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ መሪ እቅድ ላይ ግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝም፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ማእድንን የኢኮኖሚ እድገቱ ምሰሶ ብሎ ይዟቸዋል። የማዕድን ማኒስቴርም ለማዕድን ዘርፉ የተሰጠውን ይህን ትኩረት ታሳቢ በማድረግ በ2014 በጀት ዓመት የተለያዩ ተግባሮችን አከናውኗል።

አገሪቱ የማዕድን ሀብቷን በማልማት ለኢኮኖሚው እድገት የሚጠበቅበትን ድርሻ እንዲወጣ ለማድረግ ከተከናወኑ አበይት ተግባሮች መካከል የተወሰኑትን በዚህ በ2014 ዓ.ም ማጠናቀቂያ እና በ2015 ዓ.ም ዋዜማ ላይ ሆነን በምድር በረከት አምዳችን እንዳስሳለን።

ኢንቨስትመንት በተለይም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ሰላምን በእጅጉ ይፈልጋል፤ ኮሽታንም ቢሆን የሚታገስ አይደለም። ይሁንና አገሪቱ ባለፉት ዓመታት በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በአሸባሪው ሕወሓት በተደጋጋሚ በተከፈቱባት ጦርነቶችና በኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት በብዙ ፈተና ውስጥ ሆናም ኢንቨስተሮችን መሳቧን ቀጥላለች። ኢንቨስተሮችን ከሳበችባቸው ዘርፎች አንዱ ደግሞ የማዕድን ዘርፉ ነው፡፡

ለዚህም በአብነት መጠቀስ ካለባቸው መካከል በማዕድን ዘርፉ ሰገሌ በሚባለው የኢትዮጵያ ክፍል ወርቅ እና አብረው የሚገኙ ማዕድናትን ለማውጣት የሚያስችለውን ፈቃድ አግኝቶ ሥራ መጀመሩን ያስታወቀው የኖርዌዩ አኮቦ ሚኒራልስ ኩባንያ አንዱ ማሳያ ነው። የኩባንያው ኃላፊ ጆርገኝ ኤቨጄን ኢትዮጵያ የተረጋጋችና ሰላም ሆና እንዳገኟት ይገልጻሉ። ሃላፊው ኩባንያው በኢትዮጵያ በኢንቨስትመንቱ መስክ መዋዕለ ነዋይ ለማፍሰስ ሲወስን እንዴት ግጭት በተቀሰቀሰበት የጦር ቀጠና ትሄዳላችሁ የሚሉ ጥያቄዎች ከሌሎች አቻ ኩባንያዎች ቀርቦለት እንደነበር ይናገራሉ። ከእነዚሁ ኩባንያዎች አዲስ አበባ በአሸባሪው እጅ ወድቃለች የሚል የተጋነነ መረጃም ደርሷቸዋል። መረጃው ፍጹም ሃሰት እንደሆነና እንዲያውም ኢትዮጵያ ከሌሎች የማዕድን ማውጣት ሥራ ከሚካሄድባቸው በርካታ አገራት ይልቅ የተረጋጋች እና ሠላማዊ አገር እንደሆነች ኩባንያቸው በወቅቱ ማረጋገጡን ተጠቁሟል፡፡

ኃላፊው በወቅቱ በኢትዮጵያ ላይ የተቀናጁ የመገናኛ ብዙኃን የሃሰት ዘገባዎች ሲሰሩ እንደነበር አስታውሰው፣ ዘገባውን ተከትሎ በአዲስ አበባ የሚገኘው የኖርዌይ ኤምባሲ የኖርዌይ ዜጎች አዲስ አበባን ለቀው እንዲወጡ ጥሪ ማድረጉንም ተናግረዋል። ይሁን እንጂ ኤምባሲው ጥሪ ካደረገበት ቀን በፊትም ሆነ በኋላ እርሳቸውም ሆኑ ሠራተኞቻቸው ምንም የሽብርም ሆነ ያለመረጋጋት እንቅስቃሴ በመዲናዋ እንዳላስተዋሉና በስራቸው ላይ እንደሆነም ነው ያስረዱት። ማዕድን የሚያወጡበት ቦታ በአሸባሪው ቡድን ተይዞ ከነበረው አካባቢ 1 ሺህ 500 ኪሎ ሜትር እንደሚርቅ ነው ጆርገን ኤቨጄን መግለጻቸውን ፋና ብሮድካስት ኮርፖሬሽን ታህሳስ 8 ቀን 2014 ዓ.ም የዘገበውን ከማዕድን ሚኒስቴር ድረገጽ ላይ ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡

እየተጠናናቀ ያለው ዓመት ማዕድን ሚኒስቴር ከሚቀጥለው ዓመት አንስቶ የድንጋይ ከሰል በግዥ ከውጭ እንደማያስገባ ውሳኔ ላይ የደረሰበት ነበር። ይህ የሚሆነውም የውጭ ምንዛሬ በመመደብ በግዥ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን የድንጋይ ከሰል በአገር ውስጥ ምርት በመተካት ነው። ይህን ታሳቢ በማድረግም ሚኒስቴሩ በበጀት ዓመቱ ስምንት ከሚሆኑ የድንጋይ ከሰል ማዕድን ከሚያወጡ የአገር ውስጥ ኩባንያዎች ጋር ስምምነት ተፈራርሟል፡፡

ኩባንያዎቹም የድንጋይ ከሰል ማውጫ ማሽኖችን በመግዛት በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ምርት እንደሚገቡ በውል ስምምነቱ ወቅት መናገራቸውን ከሚኒስቴሩ ድረገጽ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። በወቅቱም የማዕድን ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ ኡማ እንደተናገሩት፤ የድንጋይ ከሰል እስካሁን ባለው ተሞክሮ ለሲሚንቶ አምራች ፋብሪካዎች ነበር የሚውለው። ነገር ግን የብረታ ብረት አምራች ፋብሪካዎችም 50 በመቶ የሚሆነውን የድንጋይ ከሰል በግብአትነት በመጠቀም ነው የማምረት ስራቸውን

**በጥናት ግኝቱም በኦጋዴን አካባቢ ሰባት ትሪሊዮን ኪዩቢክ ጫማ ጥልቀት ያለው የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት መኖሩ ተረጋግጧል። የጥናት ውጤቱ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት አገሪቱ ምን ያህል የተፈጥሮ ጋዝ እንዳላት ማወቅ ያስቻለ ነው። የሰርተፍኬቱ ሚና አገራችን ያላትን የተፈጥሮ ሀብት እውቀት፣ ልምድና ፍላጎት ሳይኖራቸው አንቀው ካቆዩት ኩባንያዎች በማላቀቅ ሊሰሩና ሊያለሙ ከሚችሉ ትላልቅ የውጭ ኩባንያዎች ጋር ለመሥራት ያስችላል**

የሚያከናውኑት። ወደፊት ሌሎች የብረታብረት ማምረቻ ፋብሪካዎች ሲከፈቱ ግብአቱ ስለሚያስፈልግ የድንጋይ ከሰል በአገር ውስጥ ማምረት የግድ ነው፡፡

ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ ኡማ ስምንቱንም የመግባቢያ ስምምነቱን ከፈጸሙ ማግስት ጀምሮ ወደ ሥራ በመግባት የሚያስፈልገውን ግብአት በማቅረብ የድርሻቸውን እንዲወጡ በወቅቱ አደራ ብለውም ነበር። ግብአቱ በአገር ውስጥ ተመርቶ ለፋብሪካዎቹ መቅረቡ ለድንጋይ ከሰል ግዥ በዓመት የሚወጣውን ወደ ሶስት መቶ ሚሊየን ብር ወጭ ከመቀነሱ በተጨማሪ የኃይል ግብአት ለሚፈልጉ ማንኛቸውም አምራች ኢንዱስትሪዎች ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

ለሲሚንቶ አምራች ኢንዱስትሪዎች ለኃይል ግብአት የሚውለው የድንጋይ ከሰል በበቂ ሁኔታ ማቅረብ ባለመቻሉና በዋጋ መናር ምክንያት ሲሚንቶ አምራች ኢንዱስትሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ ተቸግረው እንደነበር ሲገለጽ ቆይቷል፤ የሲሚንቶ ምርት የመሸጫ ዋጋ ከፍተኛ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች አንዱም የዚህ ግብአት በአገር ውስጥ አለመመረት መሆኑን የሚገልጹም አሉ። ችግሩ እየተጠናቀቀ ባለው በጀት አመት የተባባሰ ቢሆንም፣ ሲንከባለል የመጣ መሆኑም ይታወቃል፡፡

በማዕድን ዘርፍ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት በአገር የኢኮኖሚ እድገት ላይ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እያበረከተ ያለው የወርቅ ማዕድን እንደሆነ ይታወቃል። ይህ ትልቅ ድርሻ እንዲኖር በማድረግ ረገድ ደግሞ የባህላዊ ወርቅ አምራቾች ሚና ከፍተኛ መሆኑ ይጠቀሳሉ፡፡

ከሚኒስቴሩ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ በኩባንያዎች ተመርቶ ወደ ብሄራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን በአጠቃላይ ወደ ባንኩ ከሚገባው ወርቅ አምስት ከመቶ እንኳን አይሆንም። ወርቅ ለባንኩ በማቅረብ በኩል የላቀውን ድርሻ የያዙት ባህላዊ ወርቅ አምራቾች ናቸው። እነዚህ አምራቾች ወርቁን የሚያመርቱት በሁዋላ ቀር መንገድ ነው፤ ለጤናና ለአካባቢ ጉዳት በሚያጋልጥ እጅግ አድካሚ በሆነ ሁኔታ። በዚህ አይነት መንገድ ካመረቱት ወርቅ የድካማቸውን ያህል ገቢ እንደማያገኙም ተደጋግሞ ይገለጻል።

ማዕድን ሚኒስቴር ይህን ችግር ለመፍታትም ሰርቷል፤ አምራቾቹን ተጠቃሚ ያደርጋል ያለውን ውሳኔ ያሳለፈውም በዚሁ እየተጠናቀቀ ባለው አመት ነው። አምራቾቹ ለሚያመርቱት ወርቅ ከዓለም የወርቅ መሸጫ ዋጋ ከ10 እስከ 29 በመቶ ጭማሪ ያለው ክፍያ እንዲያገኙ ተደርጓል። የጭማሪ ማስተካከያው ለአምራቾች ገቢ ከሚያበረክተው በጎ አስተዋጽኦ በተጨማሪ ወደ ብሄራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን እንዲጨምር አስችሏል። ቀደም ሲል በህገወጥ መንገድ በሚከናወን ግብይት ምክንያት ወርቅ በሚፈለገው መጠን ወደ ባንክ አይገባም ነበር። ለውጡ የተወሰዱ የፖሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎች ውጤት እንደሆነም ከሚኒስቴሩ መረጃ መረዳት ተችሏል። በሌላ በኩልም ዘርፉ ከወቅቱ የዓለም ሁኔታ ጋር እንዲራመድ፣ ከፍ ወዳለ ደረጃ እንዲያድግ፣ተወዳዳሪም እንዲሆን ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ጋር ለመስራት ተግባራዊ እንቅስቃሴም መጀመሩን መረጃዎች ያመለክታሉ፤ ዘርፉ ከፍተኛ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲያገኝ ማዕድን ሚኒስቴር ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ከሆኑት የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ፣ አፍሪካ ልማት ባንክ እንዲሁም ከኔዘርላንድ ልማት ባንክና ከፈረንሳይ ልማት ባንክ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት ተደርጓል፤ የጂኦተርማል የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶችን በፋይናንስ ለመደገፍ ከተቋማቱ ጋር ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

በውይይቱ የገንዘብ ሚኒስትሩን አቶ አህመድ ሽዴን ጨምሮ የዓለም ባንክ፣ የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክን ከመሳሰሉ የተለያዩ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማትና አጋሮች በኢትዮጵያ የማዕድን ዘርፍ ዙሪያ መነጋገራቸውም በወቅቱ ተገጻል። በውይይቱ ኢትዮጵያ በማዕድን ዘርፍ ያላትን እምቅ አቅም በተመለከተም ለፋይናንስ ተቋማቱ ተወካዮች ገለጻ እንደተደረገላቸውና የፋይናንስ ተቋማቱ በኢትዮጵያ እየተካሄዱ ያሉ የማዕድን ፕሮጀክቶችን ለማገዝ እንዲሁም የማዕድን የግል ክፍለ ኢኮኖሚን በፋይናንስ ለመደገፍ ያላቸውን ፍላጎት መግለጻቸውም ነው የሚኒስቴሩ ማህበራዊ ድረገጽ መረጃ ያመለከተው። ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማቱ በዚህ ደረጃ ዘርፉን ከሚመራው ተቋምና ከከፍተኛ የመንግስት አመራሮች ጋር መነጋገራቸው ለዘርፉ እድገት ተስፋን ያሳድራል፡፡

የማዕድን ዘርፉን የተመለከተ አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት ክፍተቶች መኖራቸውም ሌላው በዘርፉ የሚነሳ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል። የሥነምድር ትምህርት ክፍል ያላቸው አንዳንድ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎች) መጠነኛ የሆነ ሙዝየም ቢኖራቸውም፣ አጠቃላይ አገራዊ ሀብቱን በሚዳስስ መልኩ በተደራጀ ሁኔታ ስፋት ያላቸው ሙዚየሞች አለመኖራቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ። የማዕድን ሀብቷ አይነት፣ የሀብቱ መገኛ ሥፍራዎች፣ አጠቃላይ የሆነ መረጃ አገሬውም ሆነ የዓለም ማህበረሰብ የሚያውቅበትና አይቶም አድናቆቱን ሊገልጽ የሚችልበት አልፎም ተርፎም አልምቶ ሊጠቀምበት የሚያስችል ጋለሪ (የማሳያ መዘክር) ሳይኖራት መቆየቷ በአንዳንዶች ይነሳል፡፡

አሁን ግን ማዕድን ሚኒስቴር ኢትዮጵያ የማዕድን ጋለሪ እንዲኖራት መሠረት በመጣል ክፍተቱን በመሙላት አስተዋጽኦ የሚያደርግ ተግባር ያከናወነው በዚሁ ዓመት ነው። ሚኒስቴሩም ጋለሪውን የጎበኙ የተለያዩ አካላትም የማዕድን ጋለሪውን ለአገር ትልቅ አበርክቶ ያለው ሲሉ አስተያየታቸውን በጽሁፍና በማህበራዊ ድረገጾች (ፌስቡክ) ጭምር በማስፈር አድንቀውታል፡፡

‹‹በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ››እንዲሉ፣ የጋለሪው መደራጀት የማእድን ሀብቱ በተለያየ መንገድ እንዲገለጽና ገቢም እንዲያስገኝ ዕድል የሚሰጥ መሆኑ ተስፋ አሳድሯል። የአገር ውስጥም የውጭ ኢንቨስትመንትም ለመሳብም የጎላ ፋይዳ እንዳለው ተጠቁሟል። ባለሀብቱ በጋለሪው ውስጥ በሚያገኘው መረጃ መሠረት ማእድን ለማልማትና ተጠቃሚ ለመሆን መሰማራት የሚፈልግበትን አካባቢና የማዕድን አይነት ለመለየት ሂደቱን ቀላል ያደርግለታል። ጋለሪው የቱሪስት መስህብ ሆኖ ገቢ በማስገኘት በአገር የኢኮኖሚ ዕድገት ላይም አስተዋጽኦ ያበረክታል። የአገር ገጽታን በመገንባትም ሚናው የጎላ ይሆናል። ለቱሪስቱና ለኢንቨስተሩ በጽሁፍ ማስረጃና በቃላት ከሚነገረው በላይ ማዕድናቱን በአይኑ ማየት እንዲችል መመቻቸቱ የበለጠ ትኩረትን ይስባል።

ለዘርፉ ተመራማሪዎችም መረጃ የማግኘት ድካማቸውን ከመቀነሱ በተጨማሪ የጥናት ሥራቸውን ለመለየትም ቀላል መንገድ ይሆንላቸዋል። በዘርፉ ምሁራንን የሚያፈሩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎቻቸው በቅርብ ርቀት ላይ በተግባር የተደገፈ ዕውቀት አደንዲያገኙ ያግዛቸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከምድር በታች ከሚገኘው የማዕድን ሀብቷ አንዱ የሆነው ነዳጅም ጥቅም ላይ ሳይውል ቆይቷል። ማልማት ተጀመረ ሲባል ሲቋረጥ እዚህ ተደርሷል። ተስፋ ተጥሎበት የነበረው የተፈጥሮ ጋዝ ልማትም ብዙ ርቀት ሳይጓዝ መቅረቱን መረጃዎች ያመለክታሉ።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ግን ሚኒስቴሩ በኦጋዴን አካባቢ ያለውን የነዳጅና የተፈጥሮ ሀብት አቅምና አዋጭነት ጥናት የውል ስምምነት ኤልሲኤአይ(LCAI) ከተባለው የአሜሪካ ኩባንያ ጋር አድርጎ ኩባንያውም በስምምነቱ መሰረት ጥናቱን አጠናቅቆ በማስረከብ የምሥራች አብስሯል። የጥናት ውጤቱን የሚያረጋግጥ ሰርተፍኬት ርክክብ በኩባንያውና በሚኒስቴሩ መካከል ተደርጓል፡፡

በጥናት ግኝቱም በኦጋዴን አካባቢ 7 ትሪሊዮን ኪዩቢክ ጫማ ጥልቀት ያለው የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት መኖሩ ተረጋግጧል። የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ የማረጋገጫ ሰርተፍኬቱ ምን ያህል የተፈጥሮ ጋዝ እንዳለን የምናውቅበት ነው ሲሉም ተናግረዋል። ‹‹የሰርተፍኬቱ ሚና ሀገራችን ያላትን የተፈጥሮ ሀብት እውቀት፣ ልምድና ፍላጎት ሳይኖራቸው አንቀው ካቆዩት ኩባንያዎች በማላቀቅ ሊሰሩና ሊያለሙ ከሚችሉ ትላልቅ ኩባንያዎች ጋር ለመሥራት ያስችላል›› ሲሉ በወቅቱ ተናግረዋል፡፡

የዓመቱን አንኳር ክንውኖች ያነሳነውም በ2015 በጀት አመት በእቅድ የተያዙት ለውጤት እንዲበቁና አገር በዘርፉ የምትጠብቀው እንዲሳካ በማሰብ ነው፡፡

ኢንጂነር ታከለ ኡማ የማዕድን ሚኒስትር ሆነው ሲሾሙ የአገሪቱን የማእድን ሀብት ለአገሪቱ ጥቅም ማዋል እንዲሁም ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ የሚሉት ዋና ግቦቻቸው ስለመሆናቸው መናገራቸው ይታወሳል። ‹‹የተፈጥሮ ፀጋ የሆነውን ይህን ሀብት በፍትሐዊነት ካልመራነው ለአገር የሚያበረክተው ትልቅ ሚና ወደሌላ ሊሄድ ስለሚችል የፍትሐዊነት ጉዳይ ትልቅ ትኩረት ይሰጠዋል ነበር ›› ያሉት። ዘርፉ በአስር አመቱ የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መሪ እቅድ ያለበትን ሃላፊነት እንዲወጣ፣ ኢንቨስትመንት እንዲስብና ለወጣቶችም የሥራ ዕድል እንዲፈጥር፣ አቋራጭ መንገዶችን በመዝጋት በቀጥታ ለአገር ጥቅም እንዲውል እንደሚሰሩ አስታውቀውም ነበር።

በዘርፉ የተከናወኑ ተግባሮች ይበል የሚያሰኙ ናቸው። ዘርፉ የሚጠበቅበትን እንዲወጣ ሚኒስቴሩም ሃላፊነቱን ይበልጥ ለመወጣት እንዲችል አሁንም ጠንክሮ መስራት ይኖርበታል። የድንጋይ ከሰል በአገር ውስጥ ለማምረትና ከውጭ የሚገባውን ለማስቀረት ከኩባንያዎች ጋር የተጀመሩ ስራዎች በትኩረት ሊሰራባቸው ይገባል።

የድንጋይ ከሰል በአገር ውስጥ ማምረት ፋይዳው ብዙ ብዙ ነው፤ የኢንዱስትሪዎችን የኃይል ፍላጎት ማሟላት፣ የውጭ ምንዛሬ ማዳን፣ ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር መቻል ትልቅ ነገር ነው። ይህን ሁሉ ታሳቢ በማድረግ እንዲሁም ሚኒስቴሩ በድንጋይ ከሰል ልማቱ የያዘውን እቅድ ለማሳካት አንዳንድ ኩባንያዎች ከሚኒስቴሩ የሚጠብቁት ድጋፍ ፈጥኖ ሊደረግላቸው ይገባል።

ባህላዊ የወርቅ አምራቾች የድካማቸውን ያህል ገቢ እንዲያገኙ የተከናወነው ተግባር አምራቾቹንም መንግስትንም ተጠቃሚ ያደረገ ነው፤ ምርታማነቱ ይበልጥ እንዲጨምር ግን አመራረቱን ከሁዋላቀር መንገድ ማውጣት ይገባል። ለእዚህም የማምረቻ ቁሳቁስ ድጋፍና ስልጠና መመቻቸት ይኖርበታል፤ ዘመናዊ የወርቅ ማጠቢያ ማሽኖች ባለቤት ለመሆን የሚያደርጉት ጥረትም ድጋፍን የሚፈልግ ነው። መልካም አዲስ አመት !

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ከልጅነት ድርሳን...

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

አሎምፒክ ቁርስ ቤት ሰፈራችን አስፓልቱን ተሻግሮ ያለ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የተቀባ ብቸኛው ቁርስ ቤት ነው። የቁርስ ቤቱ ባለቤት አቶ አብዱቃድር ሁሴን ይባላሉ። ሰፈር ውስጥ ማንም አብዱቃድር ብሎ የሚጠራቸው የለም። ጋሽ አብዲ ነው የሚላቸው። በረጅም ጢም ያጌጠ ጠይም ሩህሩህ ፊት አላቸው። ጉንጫቸው ዘውትር በጫት ተጎስሮ እንዳረገዘ ነው። ከወገባቸው ላይ ሽርጥ፣ ከብብታቸው ስር ጫት አይጠፋም። እግራቸው ሁሌም በነጠላ ጫማ ነው። የልጅነቴ ትልቁ ትዝታዬ ጋሽ አብዲና አሎምፒክ ቁርስ ቤት ነው። ጠዋት ማልጄም ሆነ ከሰዓት አርፍጄ ወዳሉበት ስሄድ የሚሰማኝ ደስታ ልኬት የለውም። በልጅነቴ አሎምፒክ የሚለውን ቃል ለማንበብም ሆነ ለመጥራት እንገዳገድ ነበር። ከሰፈራችን ከናሆም በቀር አሎምፒክ የሚለውን ቃል በትክክል የሚጠራ እኩያ አልነበረኝም። አብዛኛው የሰፈር ልጅ የጋሽ አብዲን የቁርስ ቤት ስም በመጥራት ነበር ጉብዝናውን የሚለካው። አንድም ቀን ግን ሳንሳሳት ጠርተነው አናውቅም ነበር።

በልጅነቴ ጋሽ አብዲ ስላሉበት ብቻ ሰፈራችን ገነትን ይመስለኝ ነበር። ቁርስ ቤቱ ሰማይ ቤት ጋሽ አብዲ ደግሞ እግዜርን ይመስሉኝ ነበር። እናቴ ዛሬም ድረስ ያልበላሁትን ጣት የሚያስቆረጥም ቁርስ ሰርታልኝ እንኳን የጋሽ አብዲን ሳንቡሳና ጭርናቄ ያክል አይጣፍጠኝም ነበር። እናቴ ብስኩት እንዳልበላ ያልነገረችኝ ተረት የለም። ዘይት ሆድ ያማል፣ ከትምህርት ሰነፍ ያደርጋል እያለች ሳንቡሳና ጭርናቄ እንድሸሽ የለፋች ቢሆንም አልተሳካላትም። ዞሬ ዞሬ መገኛዬ ጋሽ አብዲ ቁርስ ቤት ጋ ሆነ። ፈልጋ የምታገኘኝ በር ላይ ቆሜ በበላተኛ ርካታ ምራቄን ስውጥ ሆነ። ከጭርናቄ ፍቅር የተነሳ እናቴን ትምህርት ቤት ሄድኩ እያልኩ ውሎዬ እዛ ነበር።

በልጅነቴ እንደ እኛ ሰፈር ልጅ የሚበዛበት ሰፈር አልነበረም። የሆነ ደመነፍስ አለን መሰለኝ የሰፈር ልጆች ሁሉ ሳናውቀው መገኛችን ጋሽ አብዲ ቁርስ ቤት በር ላይ ነበር። የጋሽ አብዲ ቁርስ ቤት ከዳቦና ሻይ ባለፈ ብቸኛው ቴሌቪዥን ያለበት ቤትም ስለነበር ከዛ ቤት አንጠፋም። በልጅነታችን ኃይሌንና ቀነኒሳን፣ ደራርቱንና ጡርዬን የተዋወቅናቸው እዛ ቤት ነው። ልጅነቴ ያለቀው እዛ ጭርናቄ ቤት ነው ብል አበልኩ አልልም። አይ ጋሽ አብዲ..ለዛ ሁሉ የሰፈር ልጅ የሚሆን ደግነት ነበራቸው። ጋሽ አብዲ በር ላይ ቆሞ ሳንቡሳና ጭርናቄ ሳይበላ ቤቱ የሚገባ ልጅ አልነበረም። ከደግነታቸው የተነሳ ቁርስ ቤቱን የከፈቱት ድሆችን በነጻ ለመመገብ ይመስለን ነበር። ዛሬ ነው ጋሽ አብዲ ለዛ ሁሉ ለሰፈራችን ድሀ ማህበረሰብ የእግዜርን ያክል ዋጋ ያላቸው አባት እንደሆኑ የገባኝ። አድጌ ያን የልጅነት ሰፈሬን እስከለቀኩበት ጊዜ ድረስ እናቴ እጄን አንጠልጥላ ወደ ቤት የምትወስደኝ ከጋሽ አብዲ ቁርስ ቤት በር ላይ ነበር።

ማልጄ ወይም አርፍጄ ብቻ በቀናኝ በአንዴ ጭርናቄ ቤቱ በር ላይ ሆኜ እቀላውጣለሁ። ጋሽ አብዲ እስኪያዩኝ ድረስ ወዲያ ወዲህ እላለሁ..እንዲያም ሆኜ አላይ ካሉኝ ጉንፋን ያለብኝ መስዬ እስላለሁ እንዲያም ብዬ አልሰማ ካሉኝ ወደ ውስጥ ገብቼ ያልጠማኝን በባዶ ሆዴ ውሃ እጠጣለሁ። ይሄ ሁሉ በዛ በልጅነቴ ጠዋት ውስጥ ጋሽ አብዲ እንዲያዩኝ የምከፍለው መስዋዕት ነበር። አዩኝ ማለት ወይ ጭርናቄ ወይም ሳምቡሳ ይሰጡኛል። ጋሽ አብዲ አይተውኝ ዝም ያሉኝ ጊዜ የለም። እንዳዩኝ ‹አንተ ትምህርት እንዴት ነው? አባትህ ተሻለው እንዴ? እናትህስ እንዴት ናት..እቁቡን ምነው ተወችው? አንዱንም ሳልመልስላቸው ሰላሳ ጥያቄ ይጠይቁኛል። ደስ የሚለው ነገር ጋሽ አብዲ ጥያቄ ጠይቀው መልስ አይፈልጉም። የነጻነቴ ስፍራ ናቸው። አባዬ እንደሳቸው ቢሆን ስል እመኝ ነበር። አባዬ ጥያቄ ጠይቆኝ መልስ ሳይጠብቅ ቀርቶ አያውቅም። ጥያቄዎች ሁሉ መልስ አላቸው ብሎ የሚያስብ ሞገደኛ አባት ነው። አንዳንድ ጊዜ ጠይቆኝ ካልመለስኩለት ንቀት ወይም ደግሞ ትዕቢት ይመስለውና መኝታው በላይ በሰቀላት አለንጋው ይጀልጠኛል። ጋሽ አብዲ እንዲህ አይደሉም..ከጥያቄ በኋላ እጃቸው ሳይዘረጋልኝ ቀርቶ አያውቅም። አባቴ ጠይቆኝ ዝም ካልኩ በአለንጋ ነው የሚጀልጠኝ ጋሽ አብዲ ደግሞ ጭርናቄ ነው የሚሰጡኝ። ‹ማነው የሚወደኝ አባቴ ነው ወይስ ጋሽ አብዲ? ስል አስባለሁ። በልጅነቴ አባቴን በጋሽ አብዲ ልለውጠው ትንሽ ነበር የቀረኝ። ቶሎ ባላድግና ሰፈር ባንቀይር ኖሮ አባቴ ጋሽ አብዲ ናቸው ስል አዋጅ አስነግር ነበር።

በልጅነቴ ብዙ ጭርናቄ ለመብላት የጋሽ አብዲ ልጅ መሆን ያጓጓኝ ነበር። አጠገባቸው ምንጣፋቸው ቁጭ ብዬ የሚሆኑትን መሆን፣ የሚያደርጉትን ማድረግ ይናፍቀኝ ነበር። በልጅነቴ ተመኝቼ ያጣሁት ወይም ደግሞ ቀረብኝ ብዬ የምቆጭበት የጋሽ አብዲ ልጅ ሆኜ አለመፈጠሬ ነበር። አቤት ብስኩት ስወድ..አቤት ጭርናቄ ስወድ። አንዳንድ ጓደኞቼ ዶክተር ወታደር ሲሉ ግን ሳድግ እንደ ጋሽ አብዲ ጭርናቄ ቤት ከፍቼ ለመኖር ነበር የምመኘው። የጋሽ አብዲ ቁርስ ቤት ልጅነቴ ተጀምሮ ያለቀበት ስፍራ ነው። መሽቶ የሚነጋልኝ እዛ ነበር። ሁልጊዜ ጠዋት ወደዛ ስሄድ ሳምቡሳው፣ ጭርናቄው ብረት በሚመስል ነገር ላይ በላስቲክ ተሸፍኖ ሳይ ከየት እንደመጣ የማላውቀው የምራቅ ጎርፍ አፌ ውስጥ ይጎርፍ ነበር። እንዴትና ከየት እንደሚያመጡት አላውቅም። ሲጠበስ ለማየት፣ ቆሜ ለመቀላወጥ ያላደረኩት ጥረት የለም። ግን ጠዋት ደጅ ላይ ስቆም ብስኩቱ ተጠብሶ ነው የማገኘው። ዛሬም ድረስ ባልነቃሁት ጠዋት ከነ አይናሬና ከነልጋጌ ነቅቼ ወደ ጋሽ አብዲ ቤት ስሄድ ሽርጣቸውን አገልድመው፣ ጫታቸውን ብብታቸው ስር ወሽቀው በላተኛ ሲያስተናግዱ አያለሁ። ያኔ ብዙ ሀሳቦች ይመላለሱብኛል። መቼና እንዴት እንደነቁ አላውቅ እላለሁ። በዛ ሌሊት በነቃና በበቃ ሰውነት ሳያቸው አስቤ አልደርስባቸውም። በዛ ውድቅት ሌሊት እሳቸውን ሳይ እኛ ብቻ የምንተኛ ይመስለኛል። በዛ ሌሊት ካልተኙ መች ተኝተው ነቁ? ያ ሌሊት እኮ የመተኛቸው ሌሊት ነበር.. እማዬና አባዬ እንኳን አልነቁም። ጠዋት..በጣም ጠዋት ማልደው በመነሳት ጸሎት የሚያደርሱት የእማዬ አባት እንኳን ለጸሎት አልተነሱም። ጋሽ አብዲ እንዴት ተነሱ? ተኝተው የማያድሩ ሰው ናቸው ስል ደመደምኩ።

ልጅነቴ አልቆ ጎለመስኩ..ነፍስ ሳላውቅ፣ ጋሽ አብዲንም ሆነ ጭርናቄ ቤታቸውን ሳልጠግብ አገር ቀየርን። ከብዙ አመት በኋላ ወደዛ ሰፈር ተመለስኩ። እውነት ለመናገር ጋሽ አብዲን አግኝቶ እንደ ማመስገንና ትላንትን አስታውሶ እንደማውጋት ምኞት አልነበረኝም።በልጅነቴ ውስጥ ያስቀመጡት ብዙ፣ እልፍ የራሮትና የደግነት ውለታ አለ። ያን ውለታ የምመልስበት ትክክለኛ ጊዜ ላይ ስለነበርኩ ላገኛቸው ቸኩያለሁ። በልጅነቴ የማውቃቸው ጓደኞቼ እንኳን የጋሽ አብዲን ያክል አልናፈቁኝም።

ወደ ልጅነት ሰፈሬ ደርሼ ወደጭርናቄ ቤቱ አመራሁ። ያ የማውቀው አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የተቀባው ጭርናቄ ቤት አልነበረም። ትልቅ ሆቴል ተገንብቶበታል። በሆቴሉ ግራና ቀኝ የተለያዩ ዘመናዊ ሱቆች አሽብርቀውበታል። ወደውስጥ ገብቼ ስለጋሽ አብዲ ለመጠየቅ ወደ አንድ አስተናጋጅ ስንደረደር..በቅርብ ርቀት ላይ የሚያምር ሶፋ ላይ አንድ አዛውንት ተመለከትኩ። ሽርጥ ያሸረጡ፣ ረጅም ጢማቸው ቀይ ቀለም የተቀባ አዛውንት። ባለሁበት ቆምኩ ጋሽ አብዲ ስለመሆናቸው ቅንጣት ጥርጥር አልነበረኝም። እውነት እንባዬ መጣ..ሳያቸው እነዛ መስጠት የማይሰለቻቸው ደግ እጆቻቸው፣ ያቺ ለድሀ የማይቸግራት ነፍሳቸው ፊቴ ላይ አንጃበቡ። አስተናጋጁን ትቼ ወደእሳቸው ተራመድኩ። አጠገባቸው መመርኮዣ ምርኩዝ አየሁ።

አጠገባቸው ደርሼ ‹ጋሽ አብዲ? አልኳቸው። አልሰሙኝም..

ወደ ፊቴ ጎንበስ ብዬ ‹ጋሽ አብዲ? ስል ደገምኩላቸው።

ቀና ብለው አዩኝ። ያስታወሱኝ አይመስለኝም። ሁለት እጄን ሰድጄ እጃቸውን ጨበጥኳቸው። በዛ አላበቃሁም እጆቻቸውን ደጋግሜ ሳምኳቸው። በዚህም አላበቃሁም በእየሱስ እግር ላይ እንደተደፋችው መቅደላዊት ማርያም እጆቻቸው ላይ ተደፍቼ በእንባዬ አጠብኳቸው። ይሄ ሁሉ ሲሆን ምንም አላሉኝም።

ከሲቃዬ ጋር እየታገልኩ ‹አቡሌ ነኝ! አልኳቸው።

አላስታወሱኝም..ቢያስታውሱኝ እንዴት መልካም ነበር። የነፍሴን ብዙ አመት፣ የታሪኬን እልፍ ንጋት መልሼ ማን እንደሆንኩ ላስታውሳቸው ሞከርኩ። ድሮ ከድህነታቸው ላይ ቆርሰው በነጻ የሚሰጡኝን እነዛን መቼም ያልበላኋቸውን ጣፋጭ ጭርናቄዎች አስታውሼ ማን እንደሆንኩ ነገርኳቸው አላስታወሱኝም።

ሰው ደግ ልብ ሲኖረው እንዲህ ነው..ያደረገውንም የተደረገበትንም አያስታውስም።

# ዓለም አቀፍ




## በካናዳ 10 ሰዎችን በስለት ከገደሉ ተጠርጣሪዎች ሌላኛውም በፖሊስ ከተያዘ በኋላ ሕይወቱ አለፈ

በካናዳ 10 ሰዎችን በስለት ወግቶ በመግደልና 18 ሰዎች ላይ ጉዳት በማድረስ ከተጠረጠሩት ሁለት ወንድማማቾች ውስጥ አንደኛው ሞቶ ከተገኘ ከቀናት በኋላ ሌላኛውም በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ ሕይወቱ አለፈ። ፖሊስ እንዳለው የ32 ዓመቱ ማይልስ ሳንደርሰን ረቡዕ ከሰዓት በኋላ በሳስካቸዋን ግዛት ከፍተኛ ክትትል ከተደረገበት በኋላ በቁጥጥር ሥር ውሎ ነበር።

ከአካባቢው የወጣ ተንቀሳቃሽ ምስል በሮስተርን ከተማ አቅራቢያ ነጭ የስፖርት መኪና (ሱቭ) ተሽከርካሪ ከመንገድ ስትወጣ እና በፖሊስ ስትከበብ አሳይቷል። እሁድ ዕለት በተፈፀመው ጥቃት ከተገደሉት ባሻገር አስር ሰዎች ሆስፒታል የገቡ ሲሆን ሦስቱ በአስጊ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ። የግዛቷ ረዳት ኮሚሽነር ርሆንዳ ብላክሞር ረቡዕ ምሽት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫቸው፣ “ግዛታችን የእፎይታ አየር እየተነፈሰች ነው” ብለዋል።

ተጠርጣሪው ማይልስ ሳንደርሰን ቀደም ብሎ ከአንድ ግቢ ውስጥ ተሽከርካሪ እንደሰረቀ ጥቆማ እንደደረሳት የተናገረችው ረዳት ኮሚሽነሯ፣ የቤቱ ባለቤት ላይ ግን ምንም ጉዳት እንዳልደረሰ ተናግራለች። ፖሊስ በሚከታተለው ጊዜም ማይልስ 150 ኪሎ ሜትር በሰዓት እያሽከረከረ ነበር። በፖሊስ ክትትል ከመንገድ እንደወጣ በቁጥጥር ሥር ሊውል ችሏል። ማይልስ ሲያሽከረክረው በነበረው መኪና ውስጥም ስለት መገኘቱን የፖሊስ ኃላፊዋ አስታውቀዋል።

ይሁን እንጂ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ከዋለ ብዙም ሳይቆይ ማይልስ ህመም አጋጥሞት ሳስካተን ወደሚገኝ ሆስፒታል ከተወሰደ በኋላ ሕይወቱ ማለፉ ተገልጿል። ረዳት ኮሚሽነሯ ፣ የሞቱ መንስዔ ከአስከሬን ምርመራ በኋላ እንደሚታወቅ በመግለጽ ተጨማሪ ማብራሪያ ከመስጠት ተቆጥበዋል።

ቀደም ብሎ ስማቸው ያልተገለጸ ባለሥልጣን ግን ማይልስ ራሱ ላይ ጉዳት በማድረሱ መሞቱን ለአካባቢው መገናኛ ብዙኃን መናገራቸውን ቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

## አፕል ከሳተላይት ጋር መገናኘት የሚያስችለውን አይፎን 14 ስልኩን ይፋ አደረገ



አፕል ድንገተኛ የሳተላይት ግንኙነት እና የመኪና አደጋን የመለየት ቴክኖሎጂ የተገጠመለትን አይፎን 14ን በአሜሪካ በነበረው ዝግጅት ላይ ይፋ አደረገ። ኩባንያው አራት አይነት የአይፎን 14 አዳዲስ ስልኮቹን በዋና መቀመጫው ኩፐርቲኖ ያስተዋወቀ ሲሆን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ከተከሰተ በኋላም ለመጀመሪያ ጊዜ ታዳሚዎች በአካል ተገኝተዋል።

በተጨማሪም በተለይም ለስፖርተኞች የሚሆነውን አልትራ የተባለውን ሰዓቱንም አሳይቷል። በዚህ ዝግጅት ላይ በቴክኖሎጂ የላቁትን ቀጣዮቹን የአይፎን ስልኮች፣ ሰዓት እንዲሁም የማዳመጫ ምርቶቹን አሳይቷል። ኩባንያው መጠናቸው የተለያየ አይፎን 14 እና አይፎን 14 ፕላስን ለገበያ ይቀርባሉ ብሏል።

አዲሶቹ የተንቀሳቃሽ ስልኮች የአደጋ ጊዜ ጥሪ በሳተላይት መላክ የሚችሉ ናቸው። ስልኮቹ የሚያልፉ ሳተላይቶች የት እንዳሉ የሚያሳዩ ሲሆን በነሱም ላይ እንዴት በትክክል መጠቀም እንደሚቻል የሚያሳይ ቴክኖሎጂ ተገጥሞላቸዋል። መልእክት ለመላክ ከ15 ሰኮንድ እስከ ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነው የሚወስድባቸው።


“የሳተላይት ግንኙነት እንዲፈጥሩ ተደርገው የተሰሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ኢንቨስትመንቱ ዝቅ ሊደረግ አይገባም” ሲሉ የሲኤኤስ ኢንሳይት ዋና ተንታኝ ቤን ውድ ገልጸዋል። “ከሳተላይት አቅራቢው ግሎባልስታር ጋር የተደረገ የንግድ ስምምነት እና ለድንገተኛ አገልግሎት መልእክቶችን ለማስተላለፍ የሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶችን መገንባትን ጨምሮ ስልኮቹን ለመገጣጠም አፕል ዓመታት ሳይወስድበት አይቀርም።” ብለዋል።

የቴክኖሎጂ ተንታኝ ፓኦሎ ፔስካቶሬ በበኩላቸው ፈጠራው “ለመድረስ አስቸጋሪ በሆኑ አካባቢዎች” ለሚኖሩ ተጠቃሚዎች ጥሩ ዜና ነው ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል። የስልክ አምራቾች ስለ ሳተላይት አጠቃቀም ከፍ ያለ ስፍራ ሰጥተው እንዲህ የሳተላይት ግንኙነት ሲጀምሩ ማየት አበረታች ነው። በመጨረሻም አስተማማኝ እና ጠንካራ ግንኙነት አሁንም በሁሉም ተጠቃሚዎች ዘንድ በጣም ተፈላጊ መሆኑን አብራርተዋል።

ግዙፉ የቴክኖሎጂ ኩባንያ አዲሶቹ አይፎኖች ባለ 12 ሜጋ ፒክስል ካሜራ የተገጠመላቸው ሲሆን ፈጣን እንቅስቃሴ ያላቸውን ቁሶች ፎቶ ማንሳት ጨምሮ በዝቅተኛ ብርሃን ፎቶ በማንሳት ረገድ 49 በመቶ ማሻሻያ አድርጌባቸዋሁ ብሏል። አፕል እንዳለው የአይፎን ተጠቃሚዎች ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ከሶስት ትሪሊዮን በላይ ፎቶዎችን አንስተዋል።

የአይፎን 14 ዋጋ 799 ዶላር ሲሆን የአይፎን ፕሮ ደግሞ 999 ዶላር ነው። ሌላኛው አፕል ያስተዋወቀው ሲሪየስ 8 የተሰኘው ሰዓት የመኪና አደጋ መለየት፣ የወር አበባ ዑደቶችን መከታተል እንዲሁም እንቁላል የሚመረትበትን ውጳት (ኦቩሌሽን) ወቅትን የሰውነትን ሙቀት በመለካት ክትትል ማድረግን ጨምሮ በርካታ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መያዙን ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት





## የስፖርቱ ዘርፍ የአገልጋይነት ተምሳሌት

ብርሃን ፈይሳ

ስፖርት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ያደገና በስፋት መዘውተር የጀመረ ዘርፍ መሆኑን የታሪክ ማህደሮች ይነግሩናል። ከዚያ ቀደም በነበረው ጊዜ ከመደበኛ ስራቸው ጎን ለጎን የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች እንዲሁም የሰራተኛው መደብ የእረፍት ጊዜያቸውን ለማሳለፍ ነበር ስፖርታዊ ውድድሮችን የሚከውኑት። ከጊዜ በኋላ ግን ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች እየተጠናከሩና ውድድሮችም ሽልማት ማዘጋጀት መጀመራቸውን ተከትሎ የስፖርት ዘርፍን በነጻ የሚያገለግሉና በስፖርተኝነት ሙያ ሕይወታቸውን የሚመሩ በሚል ተለዩ።

መደበኛ ስራቸው ስፖርት ያልሆነ ነገር ግን ለስፖርት ባላቸው ፍቅር የተነሳ ከሜዳ፣ ከመምና ከጂምናዚየም የማይጠፉ ሰዎችም አማተር ስፖርተኞች በሚል ይጠራሉ። ‹‹አማተሪዝም›› የሚለው ቃል ሲተረጎምም በስፖርት፣ በኪነጥበብ አሊያም በሳይንስ ዘርፎች ውስጥ ባለሙያ የነበረ ነገር ግን ከጊዜ በኋላ እንደ ባለሙያ ምንም ዓይነት ገቢና ጥቅማ ጥቅም ሳያገኝ ማገልገልን ያመላክታል። ይህም በስፖርት ዘርፍ ከተለመዱ አሰራሮች መካከል ሲሆን፤ በተለያዩ ስፖርቶች መደበኛ ልምምድና ዝግጅት በማድረግ እንዲሁም በመወዳደርም ጭምር ተካፋይ ናቸው። ተሳትፏቸውም አገርን ወክለው በኦሊምፒክ እስከመወዳደር ይደርሳል።

ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ የተለመደ ባይሆንም በሌላ መልክ መተግበሩ አልቀረም። የኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ ዘርፉ በመንግስትና ህዝባዊ አካል እንደሚመራ ያመላክታል። ይህም ማለት መንግስት በበላይነት ቁጥጥር ከማድረግና አቅም የሌላቸውን ማህበራት በበጀት የመደገፍ ኃላፊነት ሲኖርበት ህዝባዊው አካል (የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት) ደግሞ ስፖርቱን ይመራል። ይኸውም ከህብረተሰቡ መካከል የተመረጡ፣ በስፖርቱ ውስጥ ያለፉ ወይም ስለ ስፖርቱ የሚያውቁ ነጻ አገልጋዮች በእውቀታቸው፣ ገንዘባቸውና በጊዜያቸው ስፖርቱንና ህዝባቸውን ያገለግላሉ። በሌላ በኩል ያለ ምንም ገቢ በገዛ ፈቃዳቸው ታዳጊ ስፖርተኞችን በማሰልጠንና በማብቃት ለክለቦች እንዲሁም ብሄራዊ ቡድኖች ግብዓት የሚሆኑ ስፖርተኞችን የሚያፈሩ በርካታ አገልጋዮችም አሉ።

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገራት ስፖርት የመልካም ገጽታቸው ምክንያት ሆኗል። ኢትዮጵያ በተለይ የታወቀችበት አትሌቲክስ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስተዋወቃት ከመሆኑም ባለፈ ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር፣ ከስፖርቱ በሚገኘው ገቢም ለሌሎች እንጀራ ሆኖ ያገለግላል። አትሌቶችና አሰልጣኞችም ታዳጊዎችን በማፍራት እንዲሁም በስፖርቱ ስር ያሉ ማህበራትን በማደራጀትና በመምራትም ያልተቆጠበ አገልጋይነታቸውን ያሳያሉ።

ለዚህ ግልጽ ማሳያ የምትሆነው ደግሞ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን በፕሬዚዳንትነት በማገልገል ላይ የምትገኘው ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ ናት። በርካቶች ‹‹አገር›› እያሉ የሚጠሯት ደራርቱ ከአገሯ አልፏ አፍሪካንም በማስጠራት ነበር የስፖርቱን ዓለም ስኬቷን የተቀዳጀችው። ለዓመታት በአትሌትነት ስታሳልፍም ላቧንም እንባዋንም ለአገሯ ያለስስት በማፍሰስ ነበር። በኦሊምፒክ፣ በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና እንዲሁም ሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮች ተካፍላ በማሸነፍና የአገርን ስም እንዲሁም ባንዲራ በበጎ በማስነሳት አገሯን ስታገለግል ኖራለች።

ከስፖርቱ ከራቀች በኋላም ወደ ፌዴሬሽኑ በመምጣት ስፖርቱንና አገሯን በአመራርነት በማገልገል ላይ ትገኛለች። በቅድሚያ በምክትል ፕሬዚዳንትነት ቀጥሎም በፕሬዚዳንትነት ፌዴሬሽኑን በመምራት ላይ የምትገኘው ፍልቅልቋ ደራርቱ አትሌቶችን፣ አሰልጣኞችን፣ ዳኞችን፣ የጽህፈት ቤቱን



ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ አገሯን በቀናነት በማገልገል በርካታ የክብር ሽልማቶችን አግኝታለች፣

ሰራተኞች እንዲሁም በስፖርቱ ዙሪያ ያሉ ባለሙያዎችን በልምዷ እንዲሁም በገንዘቧ ስታገለግል ሙሉ ጊዜዋንና ልቧን በመስጠት መሆኑን በርካቶች ይመሰክራሉ። ከአመራርነት ይልቅ እንደ አገልጋይ በልምምድና ውድድር ሜዳዎች አትሌቶችን ከማበረታታትና ከማጽናናት አልፋ እንደ እናት በመንከባከብም ጭምር ወደር የማይገኝላት አገልጋይነቷን አሳይታለች።

ከስፖርቱ ባለፈ በኢንቨስትመንት፣ በበጎ ፈቃደኝነት፣ በአስታራቂነት እንዲሁም ሰላምንና አንድነትን በማስፈን ህዝቧን እስካሁንም በማገልገል ላይ ትገኛለች። ለበርካቶች የስራ እድል በመፍጠር ረገድ በኢንቨስትመንት ተሳታፊ በመሆን ላይ ትገኛለች። ልበ ሩህሩህ በመሆኗም ካዘኑት ጋር ከማዘንና የተሰበሩትን ከማጽናናት ባለፈ የቁሳቁስ እርዳታን በማድረግ በጎ ፈቃደኝነቷንም በተለያዩ ጊዜያት አሳታለች። ሰላምና አንድነትን በመስበክና በማስታረቅ የምትተጋው እንቁ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን በአመራርነት በማገልገል እጅግ አስመስጋኝ ስራዎችን በመስራት ላይ እንደምትገኝ ይታወቃል።

በዚህም ምክንያት በርካታ እውቅናዎችን ያገኘች ሲሆን፤ በቅርቡ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተሰጣትን የክብር ዶክትሬት እንዲሁም ከቀናት በፊት በበጎ ሰው ሽልማት ላይ ልዩ ተሸላሚ ሆና ካባ ለብሳለች።

ብሔራዊ የስፖርት ፌዴሬሽኖችን መምራት አገርና ህዝብን ለማገልገል ሳይሆን አንዳች ጥቅም የሚገኝበት ስልጣን አድርገው የሚቆጥሩ በርካታ ግለሰቦች ባሉባት አገር ደራርቱ ብዙ ሸኩቻና ሴራዎችን እየታገለች የአገልጋይነት ተምሳሌት ሆናለች። ደራርቱ በፌዴሬሽን አመራርነት ዘመኗ ብዙ ፈተናዎችን ተጋፍጣለች። በስፖርቱ ውስጥ የሚፈጸሙ ሴራዎችን ተመልክታ በዝምታ አላለፈችም። ከአገር ውጤት ይልቅ ለገዛ ጥቅማቸው ቅድሚያ የሚሰጡ ግለሰቦችን ፊት ለፊት ተጋፍጣለች። በጉባኤ ፊት አልቅሳለች። አገርና ህዝብን ለማገልገል የገባችውን ቃል በሴራና በደባዎች ተሸንፋ ምን አገባኝ ብላ አልሸሸችም። ታግላ ትክክል የመሰላትን ነገር አድርጋለች። በዚህም ውጤታማ መሆኗን ሊጠናቀቅ አንድ ቀን በቀረው በዚህ አመት ብቻ በስፖርቱ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ዓለም አቀፍ ስኬቶችን በማስመዝገብ በተግባር አሳይታለች። ለዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ ለእሷ ትልቅ ክብርና ፍቅር አለው። ዛሬ የአገልጋይነት ቀን እንደመሆኑ ስፖርትና አገልጋይነት ስናስብ ከደራርቱ የተሻለ የአገልጋይነት ተምሳሌት ማንን ማስቀመጥ ይቻላል?


# የግዥ ጨረታ ማስታወቂያ

## የግዥ መለያ ቁጥር E/M/T/C/E NCB/01/2014

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ እቴጌ ምንትዋብ ንግድና ማማከር ኢንተርፕራይዝ በ2015 ዓ.ም በተፈቀደ መደበኛ በጀት ሎት አንድ የተሽከርካሪ ግዥ፣ ሎት 2 የማተሚያ ቤት ማሽነሪ ግዥ፣ ሎት ሶስት የብረታ ብረት ወርክ ሾፕ ማሽነሪ ግዥ፣ ሎት አራት የእንጨት ስራ ማሽነሪ እና ሎት አምስት የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ግዥ በዘርፉ ንግድ ፈቃድ አውጥተዉ ከተሰማሩ ህጋዊ

አቅራቢዎች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ግዥ መፈጸም ይፈልጋል፡፡

1. በዘርፉ የወጣና ለዘመኑ የንግድ ስራ ፈቃድ ኮፒ፣ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ኮፒ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰርተፍኬት ኮፒ፣ በማንኛዉም የመንግስት ግዥ ጨረታ እንዲሳተፉ በሀገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን የተሰጠ ድጋፍ ደብዳቤ ኮፒ ፈርመውና በድርጅታቸዉ ማህተም አረጋግጠው ዋናውን ማቅረብ አለባቸው፡፡
2. ማንኛዉም፣ ተጫራች የጨረታ ማስከበርያ ዋስትና የሚሆን የጠቅላላ ዋጋውን 2% ከጨረታ ሰነዳቸው ጋር በማያያዝ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በጥሬ ገንዘብ ወይም ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ ሲፒኦ ወይም በባንክ የተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ ቼክ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በእቴጌ ምንትዋብ ንግድና ማማከር ኢንተርፕራይዝ ስም አሰርተው ማቅረብ አለባቸዉ፡ በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና ጨረታው ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ከ90 ቀን በታች መሆን የለበትም፡፡
3. ተጫራቾች በተ.ቁ 1 እና 2 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በአንድ ፖስታ እንዲሁም የዋጋ መወዳደርያ ሰነዳቸዉን ኦርጅናልና ኮፒ በማለት በተለያየ ፖስታ በማሸግና በማያሻማ ሁኔታ በጀርባዉ ላይ ኦርጅናልና ኮፒ በሚል ቃል በጹህፍ በማመላከትና በድርጅታቸው ማህተም በማረጋገጥ ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. ሁሉም (ሶስቱም) ፖስታዎች በአንድ ትልቅ ፖስታ ተጠቃለዉ ታሽገዉና በድርጅቱ ማህተም ተረጋግጠው መግባት አለባቸው፡፡
5. ማንኛውም ተጫራች የተዘጋጀዉን የጨረታ ሰነድ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ እቴጌ ምንትዋብ ንግድና ማማከር ኢንተርፕራይዝ ፋይናንስና አስተዳደር ገንዘብ ያዥ ቢሮ ቁጥር 06 እንዲሁም አዲስ አበባ ካዛንችስ ከሚገኘው የዩቨርሲቲው ጉዳይ ማስፈጸሚያ ጽ/ቤት ዘወትር በስራ ሰዓት በመምጣት የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል መውሰድ ይችላሉ፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ማወዳደርያ ሰነዳቸውን በጎንደር ዩኒቨርሲቲ እቴጌ ምንትዋብ ንግድና ማማከር ኢንተርፕራይዝ ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ይህ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር እስከ 16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይችላሉ፡፡ ጨረታውም ታዛቢዎችና ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በዚሁ እለት 4፡01 ታሽጎ በእለቱ 4፡30 እቴጌ ምንትዋብ ንግድና ማማከር ኢንተርፕራይዝ ይከፈታል፡፡ ሆኖም 16ኛው ቀን የህዝብ በዓል ወይም እሁድ ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓትና ቦታ ይከፈታል፡፡
7. ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋ ጨረታው ከተከፈተ ቀን ጀምር ቢያንስ 90 ቀን ድረስ ጸንቶ መቆየት አለበት፡፡
8. ማንኛውም ተጫራች ዋጋ ሲሞላ ቫትንና ሌሎችን ታክስ እንዲሁም የትራንስፖርት ዋጋ ጨምሮ መሆን አለበት፡፡ የታክስ ሁኔታ ያልተገለጸ ከሆነ የተሞላዉ ዋጋ ማንኛውንም የመንግስት ታክስና ወጭን አካቶ እንደተሞላ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
9. ኢንተርፕራይዙ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
10. በጨረታው ለመሣተፍ የሚፈልጉ ስለ ጨረታው ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በአካል በመገኘት ወይም በስልክ ቁጥር 0908085555 በመደወል ማግኘት ይችላሉ፡፡

**የጎንደር ዩኒቨርሲቲ እቴጌ ምንትዋብ ንግድና ማማከር ኢንተርፕራይዝ**